# የኢትዮጵያ ድንበር ተሻጋሪ የኢኮኖሚ ሕግጋት ቅኝት፦ ንግድ፣ ኢንቨስትመንት እና የግልግል ዳኝነት

*ዘውድነህ በየነ ሃይሌ እና ዎን ኪዳኔ*[*]

## አህፅሮተ-ፅሁፍ

*ይህ ጽሑፍ የኢትዮጵያ ድንበር ተሻጋሪ የኢኮኖሚ ሕጎችን በተለይም ንግድን፥ ኢንቨስትመንትንና የግልግል ዳኝነትን የሚመለከቱትን ሕጎች እድገቶችንና አሁን ያሉበት ሁኔታን በጥልቀት ይመረምራል። እነዚህ የሕግ እድገቶች ግልፅ ባልሆነ ምክንያት አስቀድመው ይሁንታን ካገኙ የሕግ ሰነዶች የተለዩ መሆናቸውን በግኝቱ የዳሰሰው ይህ መጣጥፍ፤ ተቀባይነት ያለው፥ ምክንያታዊ፥ ሊረጋገጥ የሚችል እና ለሙግት የሚመች ኢኮኖሚያዊ፥ ማህበራዊና ሌሎች ዓላማዎችን ለማሳካት ሲባል ልዩነቶችን መቀነስ እንደሚገባ ምክረሀሳብ ይሰጣል።*

## መግቢያ

ምንም እንኳን ስያሜው በግርድፉ አሳሳች ቢመስልም በድንበር ተሻጋሪ የኢኮኖሚ መስተጋብሮች ላይ ተፅእኖ ያላቸው የተለያዩ ሕጎች ለምርምርና ለፖሊሲ ትንተና ሲባል በጥቅሉ ድንበር ተሻጋሪ የኢኮኖሚ ሕግጋት በመባል ይጠራሉ።[1] ይህንን መሰረት በማድረግ

---

[*] ዶ/ር ዘውድነህ በየነ ሃይሌ እና ፐ/ር ዶ/ር ዎን ለማ ኪዳኔ ዋና መቀመጫውን በአሜሪካን አገር በዋሽንግተን ዲ.ሲ. ያደረገውና በዓለም አቀፍ የንግድና የኢንቨስትመንት የግልግል ዳኝነት እንዲሁም በሌሎች ድንበር ተሻጋሪ በሆኑ ዓለም አቀፍ የሕግ ጉዳዮች ላይ ዓለም አቀፍ የጥብቅና እና የማማከር አገልግሎትን በመስጠት የሚታወቀው የአዲስ ሎው ግሩፕ ኤል. ኤል. ፒ. (ኤ. ኤል. ጂ.) [ADDIS LAW GROUP LLP – ALG] መስራቾች እና ሃላፊዎች ናቸው። ለበለጠ መረጃ የጥብቅና ድርጅቱን ድረ ገፅ www.addislawgroup.com ይመልከቱ።

[1] በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ “ድንበር ተሻጋሪ ሕግ (transnational law)” የሚለው ቃል አገባብ ፊሊፕ ጄሰፕ እ.አ.አ. በ1950ዎቹ ባደረገው ንግግሩ ውስጥ እንደተጠቀመዉ ነው። The term ‘transnational law’ … includes “all law which regulates actions or events that transcend national frontiers. Both public and private international law are included, as are other rules which do not wholly fit into such standard categories.” “[ድንበር ተሻጋሪ ሕግ ማለት] ከሀገራዊ ድንበሮች በላይ የሆኑ ድርጊቶችን ወይም ክስተቶችን የሚገዛ ሕግ ነዉ። በተጨማሪም ዓለም አቀፍ እና የግል ዓለም አቀፍ ሕጎችን፣ እንዲሁም ከእንደነዚህ ዓይነት መደበኛ የሕግ ምድቦች ጋር ሙሉ በሙሉ የማይገጥሙ ሌሎች ሕጎችንም ያካትተታል።” Jessup 1956 lectures at Yale Law School, quoted in: Peer Zumbansen, Transnational Law in Jan Smits (ed.), Encyclopedia of Comparative Law. pp. 738-754 (Edward Elgar Publishing: 2006) at. 738. Text available at

ይህ መጣጥፍ የኢትዮጵያን ድንበር ተሻጋሪ የኢኮኖሚ ሕግጋት ምንጮችን በመለየት በተመረጡና አስፈላጊ ተብለው በተለዩ ይዘቶቻቸው ላይ ሂሳዊ ምዘናን ይሰጣል። ይህ የሕግ ዘርፍ ንግድን፤ ኢንቨስትመንትንና የአለመግባባት መፍቻ ዘዴን በተለይም የግልግል ዳኝነትን ያካትታል።

## 1. የኢትዮጵያ የንግድ ስምምነቶችና ደንቦች

ኢትዮጵያ ባመዛኙ ውስብስብ ከሆነው የዓለም አቀፍ ንግድ ስርዓት ውጭ ራሷን አስቀምጣለች። ምንም እንኳን የዓለም አቀፍ ንግድ ድርጅት አባል ለመሆን አርፍዳም ቢሆን ፍላጎቷን በመግለፅ ሂደቱን የጀመረች ቢሆንም[2] እስካሁን ድረስ እዚህ ግባ የሚባሉ አስገዳጅ የሁለትዮሽ የንግድ ስምምነቶች ያላት አገር አይደለችም። ንግድን የተመለከቱና ኢትዮጵያ አባል የሆነችባቸው ዓለም አቀፍ የሕግ ስምምነቶች የሚከተሉት ናቸው።

(1) እ.ኤ.አ. በኖቬምበር 5 ቀን 1993 በካምፓላ የተፈረመው የምስራቅና ደቡባዊ አፍሪካ የጋራ ገበያ ማቋቋሚያ ዓለም አቀፍ ስምምነት፤

(2) እ.ኤ.አ. በማርች 1996 በናይሮቢ የተፈረመው የበይነ-መንግስታት የልማት ድርጅት (“ኢጋድ”) ማቋቋሚያ ዓለም አቀፍ ስምምነት፤

(3) እ.ኤ.አ. በጁን 23 ቀን 2000 በኮቶኑ የተፈረመው የአፍሪካ፣ ካሪቢያንና የፓስፊክ ቡድን አገራት ከአውሮፓ ሃገራት ጋር የተፈራረሙት የኢከኖሚ ትብብር ስምምነት፤

(4) የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና ስምምነት፤ እና

(5) የአህጉሩ 54 አገሮች በአባልነት የሚገኙበትና የአፍሪካን የኢኮኖሚ ማሕበረሰብ ለመገንባት ያለመው የአቡጃ ዓለም አቀፍ ስምምነት[3]።

---

https://digitalcommons.osgoode.yorku.ca/cgi/viewcontent.cgi?referer=https://scholar.google.com/&httpsredir=1&article=1181&context=clpe

[2] ከአስር አመታት በላይ ተስተጓጉሎ የነበረው ኢትዮጵያ የዓለም አቀፍ ንግድ ድርጅትን ለመቀላቀል የምታደርገው ድርድር እ.አ.አ. በ2019 እንደገና ተጀምሯል። ይህ ጽሑፍ በሚፃፍበት ጊዜ የመሳካት ወይም ያለመሳካት ዕድሉ ግልፅ አልነበረም። ለበለጠ መረጃ ይኸን ፅሁፍ ይመልከቱ፡- International Trade Administration (ITA), Ethiopia: Country Commercial Guide at https://www.trade.gov/knowledge-product/ethiopia-trade-agreements

[3] ንግድን የተመለከቱና ኢትዮጵያ አባል የሆነችባቸው ዓለም አቀፍ የሕግ ስምምነቶች እነዚህ ብቻ እንደሆኑ በITA ተገልጿል። https://www.trade.gov/knowledge-product/ethiopia-trade-agreements. የኢትዮጵያ ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ድረ-ገጽ በዚህ ጉዳይ ላይ ተጨማሪ መረጃ የለውም። የኢትዮጵያ ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ድረ-ገጽ ይመልከቱ። http://www.motin.gov.et/home

**ኢትዮጵያ ድሃ ከሚባሉ አገሮች ተርታ የምትመደብ በመሆኗም አሜሪካ[4]፣ የአውሮፓ ህብረትንና[5] ቻይናን[6] ጨምሮ ቀዳሚ ከሚባሉ የንግድ አጋሮች በልዩ ሁኔታ ድጋፍ ታገኛለች።**

---

[4] Office of the United States Trade Representative, The African Growth and Opportunity Act *(*AGOA*)*, USTR.GOV, https://ustr.gov/issue-areas/trade-development/preference-programs/african-growth-and-opportunity-act-agoa [https://perma.cc/Y8JY-C8AH].

> Since its enactment in 2000, the African Growth and Opportunity Act (AGOA) has been at the core of U.S. economic policy and commercial engagement with Africa. AGOA provides eligible sub-Saharan African countries with duty-free access to the U.S. market for over 1,800 products, in addition to the more than 5,000 products that are eligible for duty-free access under the Generalized System of Preferences program.
>
> **(እ.ኤ.አ. በ2000 ከፀደቀበት ጊዜ ጀምሮ** AGOA **አሜሪካ ከአፍሪካ ጋር ላላት የኢኮኖሚ ፖሊሲ እና የንግድ ግንኙነት አስኳል ነው። በ**Generalized System of Preferences program **መሰረት ከቀረጥ ነፃ ከሆኑ 5,000 በላይ ምርቶች በተጨማሪ** AGOA **ከሰሃራ በታች ካሉ የተመረጡ የአፍሪካ ሀገራት ለሚመጡ ከ1,800 በላይ ምርቶች በአሜሪካ ገበያ ከቀረጥ ነፃ ዕድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ አድርጓል።)**

[5] **ይኽን ፅሁፍ ይመልከቱ**:- EU Trade Policy and Africa's Exports, at https://trade.ec.europa.eu/doclib/docs/2017/november/tradoc_156399.pdf

> The EU is the most open market for African exports. Most African countries have fully free access to the EU market. Other partners offer less favourable conditions for African exports. Europe is by far Africa's largest export market and its main customer. Thanks to EU trade openness, exports of food and manufactured products from Africa to the EU keep increasing.
>
> **(የአውሮፓ ህብረት ለአፍሪካ ወጪ ንግድ በጣም ክፍት ገበያ ነው። አብዛኛዎቹ የአፍሪካ ሀገራት በአውሮፓ ህብረት ገበያ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ከቀረጥ ነፃ ዕድል ተጠቃሚ ናቸው። ከሌሎች የአፍሪካ አጋሮች አንፃር የአውሮፓ ህብረት ገበያ ለአፍሪካ የወጪ ንግድ በይበልጥ ምቹ ነው። አውሮፓ እስካሁን ለአፍሪካ ትልቁን የኤክስፖርት ገበያ እንዲሁም ዋና ደንበኛ ነው። ለአውሮፓ ህብረት ገበያ ክፍትነት ምስጋና ይግባውና ከአፍሪካ ወደ አውሮፓ የሚላከው ምግብ እና በፋብሪካ የተመረቱ ቁሳቁሶች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ነው።)**

[6] **ይኽን ፅሁፍ (ገፅ 21) ይመልከቱ**:- From China-Africa to Africa-China: A Blueprint for a Green and Inclusive Continent-Wide African Strategy towards China, at https://developmentreimagined.com/wp-content/uploads/2021/06/blueprint-final-14.06.pdf

> In 2010, China agreed to allow imports from Least Developed Countries (LDCs) under a Duty-Free Quota Free Scheme (DFQF). This scheme was renewed in 2015 and is estimated to cover 97% of tariff lines. However, it has had a limited impact so far. For example, while 99% of all LDC imports into China in 2011 were under the DFQF scheme, China has imported little beyond such commodities from African

**ምንም እንኳን ኢትዮጵያ ዘለግ ያለ የገቢ ንግድ የቀረጥ ስርዓትን** (import tariff schedules)[7] **ብትቀርፅም፤ የአሜሪካ የዓለም አቀፍ ንግድ አስተዳደር እንደሚጠቁመው የእነዚህ ደንቦች ዓላማ "ገቢን ለማሳደግ እንጂ የሃገር ውስጥ ምርቶችን ለመጠበቅ አይደለም"።** [8] **በመሆኑም የኢትዮጵያን የቀረጦች አጣጣል ስርዓት አስመልክተው በውጭ አስተያየት የሚሰጡ አካላት ኢትዮጵያን የሚስሏት እርሷ አባል በሆነችባቸው አህጉራዊ (ቀጣናዊ) የንግድ ስምምነቶች መሰረት ከተቀረፁት ጥቂት የቀረጥ ስርዓቶች በስተቀር እጅጉን የተጋነነ የገቢ ማስገኛ ስርዓትን የዘረጋች አገር እንደሆነች ነው።** [9]

---

LDCs. The WTO largely attributes under-utilization of these preference schemes to complex Rules of Origin (ROOs), market access challenges and direct transportation requirements.

**(እ.ኤ.አ. በ** 2010 ***ቻይና በቀረጥ-ነጻ ኮታ-ነፃ መርሃ ግብር*** (DFQF) **ካልበለፀጉ *ሀገራት*** (LDCs) ***ምርቶች እንዲገቡ ፈቅዳለች። ይህ እቅድ እ.ኤ.አ. በ***2015 ***ታድሷል፤*** 97% ***የታሪፍ ምድቦችን ይሸፍናል ተብሎ ይገመታል። ሆኖም ግን እስካሁን ያለው ተፅዕኖ ውስን ነው። ለምሳሌ እ.ኤ.አ. በ***2011 ***ከመላው የ***LDC ***ወደ ቻይና ከገቡት ምርቶች ውስጥ*** 99% ***ያህሉ በ***DFQF ***እቅድ ስር ሲሆኑ፣ ቻይና በራሷ ፍላጎት ከአፍሪካ*** LDC ***ከእንደነዚህ አይነት ሸቀጦች ውጪ ሌላ አላስገባችም ማለት ይቻላል። ለዚህም የአለማቀፍ ንግድ ድርጅት እንደ ዋና ምክንያት ያቀረባቸው የልዩ ተጠቃሚነት ዕድል ጋር በተያያዘ የሸቀጦችን መነሻ የሚደነግጉ ውስብስብ ደንቦች*** (ROOs)፣ ***የገበያ ተደራሽነት ተግዳሮቶች እንዲሁም ሸቀጦችን በሶስተኛ ሀገር በኩል ሳይሆን በቀጥታ የመጓጓዣ መስፈርቶችን ነው።)***

[7] ***ለምሳሌ ይህን መረጃ ይመልከቱ፡-*** https://customs.erca.gov.et/trade/customs-division/tariff?lang=en

[8] International Trade Administration (IAT), Ethiopia: Country Commercial Guide at https://www.trade.gov/knowledge-product/ethiopia-import-tariffs

[9] ***ዝኒ ከማሁ።***

Revenue generation, not protection of local industry, appears to be the primary purpose of Ethiopia's tariffs. Goods imported from the Common Market for Eastern and Southern Africa (COMESA) members are granted a 0 to 10% tariff preference, (depending on the type of goods) under the Free Trade Agreement (FTA). Tripartite FTA membership among COMESA, the South African Development Community (SADC), and the East African Community (EAC) members will allow zero tariffs and duties, which will impact Ethiopian trade when it completes the COMESA accession process (timeline for completion is unclear). Customs duties are payable on imports by all persons and entities that have no duty-free privileges. In 2019 Ethiopian customs ceased its policy of reducing, or eliminating, customs duties on imports of knocked-down and semi knocked-down industrial inputs. This new revision has reclassified these products to be treated with basic tariff rates.

***(የኢትዮጵያ ታሪፍ ዋና ዓላማ ገቢ ማመንጨት እንጂ የሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪ ጥበቃ አይመስልም። በነጻ የንግድ ስምምነት*** (FTA) ***መሠረት ከምሥራቅና ደቡብ አፍሪካ የጋራ ገበያ*** (COMESA) ***አባል***

## 2. የኢትዮጵያ የኢንቨስትመንት ሕግ

ከዚህ ቀደም የተደረጉ ጥናታዊ ፅሁፎች በቅርቡ (እ.አ.አ. በ2020) እስከወጣው የኢንቨስትመንት አዋጅና ደንብ ድረስ የነበረውን ጊዜ በማካተት የኢትዮጵያ የኢንቨስትመንት ሕግ ምንጮች፣ ዕድገትና ይዘቶች ላይ ትንተናን ሰጥተዋል።[10] ይህ ክፍል አሁን ባለው ሕግ ላይ ያተኩራል።

### 2.1. ዓለም አቀፍ ስምምነቶች

ኢትዮጵያ 34 የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን የተፈራረመች ስትሆን፤ ከነዚህ ውስጥ 21 ስምምነቶች ብቻ በስራ ላይ የሚገኙ ናቸው።[11] እንደ መንደርደሪያ ባለፉት 4 ዓመታት ኢትዮጵያ ቢያንስ 10 የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ብትፈርምም፤ አንዳቸውም ፀድቀው ወደ ስራ አለመግባታቸውን ማንሳቱ ጠቀሚታ አለው።[12]

ሀገራት የሚገቡ ዕቃዎች እንደየ እቃው አይነት ከ0 እስከ 10 በመቶ የታሪፍ ቅነሳ ልዩ ዕድል ተሰጥቷቸዋል። የCOMESA፣ የደቡብ አፍሪካ ልማት ማህበረሰብ (SADC) እና የምስራቅ አፍሪካ ማህበረሰብ (EAC) አባል ሀገራት መካከል የሶስትዮሽ የነፃ ንግድ ስምምነት ዜሮ ታሪፍ እና ቀረጥ ይፈቀዳል። ይሄም ኢትዮጵያ COMESAን የመቀላቀል ሂደት ካጠናቀቀች በኋላ በሀገሪቷ ንግድ ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል (የሂደቱ መጠናቀቂያ ጊዜም ግልፅ አይደለም)። ከቀረጥ ነፃ መብት የሌላቸው ሰዎች እና አካላት ወደ ሀገር ውስጥ ለሚያስገቧቸው እቃዎች የጉምሩክ ቀረጥ ይከፍላሉ። እ.ኤ.አ. በ2019 የኢትዮጵያ ጉምሩክ ከውጭ በሚገቡ በከፊል አሊያም ሙሉ ለሙሉ ባልተገጣጠሙ የኢንዱስትሪ ግብአቶች ላይ የጉምሩክ ቀረጥ የመቀነስ ወይም የማስቀረት ፖሊሲውን አቁሟል። ይህ አዲስ አሰራር እነዚህን ምርቶች በመሠረታዊ የታሪፍ ስሌት እንዲስተናገዱ አድርጓል።)

[10] Won Kidane, The Legal Framework for the Protection of Foreign Direct Investment in Ethiopia, Chapter 26, in THE OXFORD HANDBOOK OF THE ETHIOPIAN ECONOMY (Cheru, et al, ed. OUP, 2019).

[11] ይህን ዳታቤዝ ይመልከቱ፡- Bilateral Investment Treaties (BITs) that Ethiopia signed at https://investmentpolicy.unctad.org/international-investment-agreements/countries/67/ethiopia [hereinafter Ethiopia BITs] [https://perma.cc/BB72-C4LL].
ዳታቤዙ 35 ስምምነቶችን ያሳያል። ነገርግን በ1964 የተፈረመው የኢትዮጵያ-ጀርመን የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ስምምነት ተቋርጦ በ2004ቱ ስምምነት ተተክቷል። ከዚህም በተጨማሪ ኢትዮጵያ ከህንድ እና ደቡብ አፍሪካ ጋር የተፈራረመቻቸው የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ስምምነቶች በሃገራቱ በተናጠል ተቋርጠዋል። ዝኒ ከማሁ።

[12] ዝኒ ከማሁ። እነዚህ አራት የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ስምምነቶች ከ2016 ጀምሮ ተፈርመዋል። በ2009 እና 2016 መካከል ምንም የሁለትዮሽ የኢንቨስትምነተ ስምምነት አልተፈረመም። ዝኒ ከማሁ።

ይህ የሆነው ህንድና[13] ደቡብ አፍሪካ[14] የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ላይ የያዙትን ጥርጣሬና የአቋም ለውጥ ለመከተል ታስቦ፤ ወይም ደግሞ በአስተዳደራዊ ዳተኝነት አሊያም በቢሮክራሲ ልግመት እንደሆነ በግልፅ አይታወቅም።

የኢትዮጵያ የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ፕሮግራም ታሪክ[15] ረጅም ዘመንን ያስቆጠረ ነው። የተጀመረውም ኢትዮጵያ የመጀመሪያውን የኢንቨስትመንት ሕጓን[16] እ.አ.አ. በ1964 ካፀደቀች ከአንድ ዓመት በኋላ እ.አ.አ. በ1964 ነው። እ.አ.አ. በ1964 ከጀርመን ጋር የተፈራረመችው የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ዓለም አቀፍ ስምምነት[17] በዓለማችን ከተደረጉት የመጀመሪያዎቹ ተርታ የሚመደብ ነው። በዓለም የመጀመሪያው

---

[13] በተከታታይ የኢንቨስትመንት የግልግል ጉዳዮች ኪሳራ ቅር የተሰኘችው ህንድ በጊዜው የነበሯትን የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ስምምነቶች በሙሉ በመካድ የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ስምምነቶች በአዲስ ሞዴል መዋዋል ጀመረች። ስለ ህንድ የኢንቨስተርና የመንግስት አለመግባባት መፍቻ ስርአት (ISDS) እንዲሁም በአዲስ ሞዴል የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ስምምነቶችን እንደገና ለመደራደር የምታደርገውን ጥረት የበለጠ ለመረዳት ይህን ፅሁፍ ያንብቡ፡- Won Kidane, *China's* and *India's* Differing Investment Treaty and Dispute Settlement Experiences and Implications for Africa, LOYOLA UNIVERSITY CHICAGO LAW JOURNAL, Vol. 49, 406-474 (2017) at pp. 445-461.

[14] ምንም እንኳን ደቡብ አፍሪካ እንደ ህንድ የኢንቨስትመንት ግልግል እክሎች ባያጋጥሟትም፣ ተመሳሳይ ተፈጥሮ ያላቸው ችግሮች ሊያጋጥሙ ይችላሉ በሚል ስጋት አጠቃላይ የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ስምምነቶች አሰራርን እንደገና እንድታሰብ አድርገዋል። ለዝርዝሩ ይህን ፅሁፍ ያንብቡ፡- Won Kidane, Contemporary International Investment Law Trends and *Africa's* Dilemmas in the Draft Pan-African Investment Code, GEORGE WASHINGTON INTERNATIONAL LAW REVIEW, Vol. 50, 523-579, at 557-561.

[15] ከሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ስምምነቶች በተጨማሪ UNCTAD የሚከተሉትን የውጪ ኢንቨስትመንትን በተመለከተ ጉልህ አንድምታ ያላቸውን የሕግ ሰነዶች ይዘረዝራል፡- MIGA Convention1985, UN Code of Conduct on Transnational Corporations (1983), World Bank Investment Guidelines (1992), ILO Tripartite Declaration on Multinational Enterprises (2006), UN Guiding Principles on Business and Human Rights (2011), Permanent Sovereignty UN Resolution (1962), New International Economic Order UN Resolution (1974), Charter of Economic Rights and Duties of States (1974). ለበለጠ መረጃ የሚከተለውን ይመልከቱ፡- https://investmentpolicy.unctad.org/international-investment-agreements/countries/67/ethiopia

[16] Decree No. 51 of 1963, Decree to Provide for the Encouragement of Capital Investment in Ethiopia, INTERNATIONAL LEGAL MATERIALS, Vol. 3, No. 1 (January 1964), pp. 41-44.

[17] Treaty between the Federal Republic of Germany and the Empire of Ethiopia concerning the Promotion of Investments, Ger.-Eth., 1964. [ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት በየጀርመን ፌደራል ሪፐብሊክና በኢትዮጵያ መካከል የተፈረመ የሁለትዮሽ ዓለም አቀፍ ስምምነት፥ እ.ኤ.አ. 1964። [ከዚህ በኋላ የ1964 ኢትዮ-ጀርመን ስምምነተ እየተባለ የሚጠቀስ]]። የዚህ ስምምነት የእንግሊዝኛው ቅጂ እዚህ ድረ-ገፅ ላይ ይገኛ https://investmentpolicy.unctad.org/international-investment-agreements/treaty-files/1165/download

በመሆኑ ከሚታወቀውና እ.አ.አ. በ1959 በጀርመንና በፓኪስታን መካከል ከተፈረመው የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ዓለም አቀፍ ስምምነት[18] ጋር ኢትዮጵያና ጀርመን እ.አ.አ. በ1964 የተፈራረሙት ስምምነት አንድ ዓይነት ነው።

የጀርመኑ ሞዴል መሰረታዊ የሚባሉትን አብዛኞቹን የኢንቨስተር (ባለሀብት) ጥበቃ መርሆዎችን በግርድፉ የያዘ ነው።[19] ያልተጠበቀ ባይሆንም ሞዴሉ በመንግስታት መካከል ሊኖር ስለሚችል የአለመግባባት መፍቻ ስርዓትን ቢተልምም በባለሀብትና በመንግስት መካከል የሚኖር አለመግባባት የሚፈታበትን ስርዓት አላካተተም።[20]

ኢትዮጵያ ሁለተኛውን የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ዓለም አቀፍ ስምምነት የተፈራረመችው ሶስት አስርት ዓመታትን ካሳለፈች በኋላ እ.አ.አ. በ1994 ከጣሊያን ጋር ነው።[21] ይህ ከጣሊያን ጋር የተፈረመው የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ዓለም አቀፍ ስምምነት በስራ ላይ የዋለ የመጀመሪያው ስምምነት ነው። በስራ ላይ የዋለውም እ.አ.አ. በሜይ 1998 ነው።[22] በዛን ዘመን የነበሩ የሕግ ዕድገቶች ለድንበር ተሻጋሪ የኢኮኖሚ ጉዳዮች ቅድሚያ አይሰጡም ነበር ቢባል ማጋነን አይሆንም። እ.አ.አ. የ1990ዎቹና የ2000ዎቹ አስርት ዓመታት ግን የዓለም አቀፍ ስምምነቶች መፈራረም በፍጥነት ያደገበትና በተጓዳኝም ብሔራዊ ህግጋትን የመደንገግ ጉልህ ጥረቶች የተደረጉባቸው ናቸው።[23] የኢትዮጵያ 21 የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በስራ ላይ የዋሉትም እ.አ.አ. በ1997 እና በ2010 ባሉት ጊዜያት መካከል ነው።[24]

[18] በዓለም ላይ የመጀመሪያው እንደሆነ የሚታመነው የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ስምምነት በጀርመን እና በፓኪስታን መካከል በ1952 ተፈርሞ በ1962 ተፈፃሚ ሆኗል። ሰነዱ በዚህ ድረ-ገፅ ይገኛ https://investmentpolicy.unctad.org/international-investment-agreements/treaties/bilateral-investment-treaties/1732/germany---pakistan-bit-1959-

[19] ኢትዮ-ጀርመን ስምምነት፥ *በግርጌ ማስታወሻ ቁ. 17* የተጠቀሰ፥ አንቀጽ 2 (አድልዎ አለመፈፀም) እና አንቀጽ 3 (ደህንነትና ጥበቃ እና ንብረት አለመውረስ)።

[20] ኢትዮ-ጀርመን ስምምነት፥ *በግርጌ ማስታወሻ ቁ. 17* የተጠቀሰ፥ አንቀጽ 11 (አለመግባባቶችን መፈቻ ስርአት)።

[21] ስለ የኢትዮጵያ-ጣሊያን የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ስምምነት መፈረም (signature) እዚህ ይመልከቱ፡- https://investmentpolicy.unctad.org/international-investment-agreements/countries/67/ethiopia

[22] ስለ የኢትዮጵያ-ጣሊያን የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ስምምነት መፅደቅ (ratification) እዚህ ይመልከቱ፡- https://investmentpolicy.unctad.org/international-investment-agreements/countries/67/ethiopia

[23] አሁን ተፈፃሚነት ስላላቸው የሀገር ውስጥ ሕጎች ገለፃ ከታች ንዑስ-ክፍል 3.2. ይመልከቱ።

[24] የመፅደቅ (ratification) ሁኔታን ለማወቅ ይህን ድረ-ገፅ ይመልከቱ

ሁሉም በሚባል መልኩ የዓለም አቀፍ ስምምነቶቹ “ከአድልዎ የነፃ” (non-discrimination)፥ “ፍትሃዊና ሚዛናዊ አገልግሎት” (fair and equitable treatment)፥ “የማይወረስ” (non-exporpriation)፥ እና “በባለሀብትና በመንግስት መካከል የሚደረግ ያለመግባባት መፍቻ ስርዓትን” (Investor-State Dispute Settlement-ISDA) የሚባሉ የኢንቨስትመንትና የባለሀብት ጥበቃ መሰረታዊ የሆኑ መርሆዎችን ያካተቱ ናቸው። [25]

ከእነዚህ ምንጫቸው ድንበር ተሻጋሪ ከሆኑ ሕግጋት የ21 አገራት ባለሀብቶች[26] የሕግ ከለላን ያገኛሉ። ባለሀብቶቹ በተጨማሪነት የሚያገኟቸው ጥቅሞች ባህርይና ስፋት እንደስምምነቶቹ አንቀፆች አቀራረፅ ይለያያል። የስምምነቶቹ አንቀፆች በተመሳሳይ ስለሚነበቡ ብቻ ጥበቃዎቹም አንድ ዓይነት ናቸው ብሎ መደምደም አይቻልም። እንዲያውም በተቃራኒው በአንቀፆቹ አቀራረፅ ላይ የሚታዩ ጥቂት ልዩነቶች በአለመግባባት የመፍቻ ክርክሩ ላይ ከፍተኛ ልዩነትን የሚፈጥሩ ሊሆኑ ይችላሉ።

የኢትዮጵያ የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ታሪክ በግልፅ በሚታይ መልኩ ባደጉና በታዳጊ አገሮች (North-South) ወይም በታዳጊ አገሮች (South-South) መካከል የሚለውን የተለምዶ ድልድል የሚያፈርስ ነው። ለዚህም ምክንያቱ ግማሾቹ ስምምነቶች ከታዳጊ ኢኮኖሚዎች ለምሳሌም ከየመን፣ ሊቢያና ሱዳን ጋር የተደረጉ ሲሆን፤ ቀሪዎቹ እኩሌታዎች ደግሞ ከበለፀጉ ኢኮኖሚዎች፥ ለምሳሌም ከኔዘርላንድስ፣ ስዊድንና ጀርመን ጋር የተደረጉ በመሆናቸው ነው። [27] ይህም አንድርያስ ሎወንፊልድ በጣሙን ተሰሚ በሆነ መልኩ የዓለምአቀፍ ኢንቨስትመንት ሕግ ስረ መሰረቱ የቅኝ አገዛዝ ህግን መተካት ነው በማለት እንደሚከተለው የሚያጠነጥነውን ሀሳብ የሚደግፍ አይደለም።

---

https://investmentpolicy.unctad.org/international-investment-agreements/countries/67/ethiopia

[25] ለንጽጽራዊ ትንተና ጥሩ ናሙና የሚሆኑት የመጀመርያው የኢትዮጵያ-ኩዌት (1998) ስምምነት እና የቅርብ ጊዜ የሆነው የኢትዮጵያ-ግብጽ (2010) ስምምነት ነው። ሁለቱም ከዚህ ድረ-ገፅ ላይ ይገኛሉ፡- https://investmentpolicy.unctad.org/international-investment-agreements/countries/67/ethiopia. ምንም እንኳን አይነታዊ ክፍፍል ቢኖርም መሰረታዊ ህጎች ግን ተመሳሳይ ናቸው።

[26] ግብጽ (2010)፣ ፊንላንድ (2007)፣ ስዊድን (2005)፣ ኦስትሪያ (2005)፣ ሊቢያ (2004)፣ ጀርመን (2006)፣ እስራኤል (2006)፣ ኢራን (2004)፣ ፈረንሳይ (2004)፣ ኔዘርላንድ (2005)፣ አልጄሪያ (2005)፣ ዴንማርክ (2005)፣ ቱኒዚያ (2004)፣ ቱርክ (2005)፣ ሱዳን (2001)፣ የመን (2000)፣ ማሌዥያ (1999)፣ ስዊዘርላንድ (1998)፣ ቻይና (2000)፣ ኩዌት (1998) እና ጣሊያን (1997) በ UNCTAD መዘርዝር መሠረት በቅደም ተከተል ተዘርዝረዋል። https://investmentpolicy.unctad.org/international-investment-agreements/countries/67/ethiopia

[27] ዝኒ ከማሁ።

*በአፍሪካና በእስያ የተወሰኑ አገራት የነበረውን ከቅኝ አገዛዝ ነፃ የመውጣት ማዕበልና በሁሉም የሶስተኛው ዓለም አገሮች ይካሄድ የነበረውን የውጭ አገር ባለሀብቶችን ኢንቨስትመንቶች የመውረስ ማዕበልን ተከትሎ በ1960ዎቹ የመጀመሪያ ዓመታት ላይ በኢንቨስትመንት ተቀባይ አገሮች ላይ ለሚጣል ግዴታ ስምምነትን ማግኘት አዳጋች እንደሚሆን ግልፅ ሆነ። ዓለም አቀፍ እርዳታን በመስጠት ቀዳሚ የሆነው የዓለም ባንክም ባንድ በኩል የውጭ ባለሀብቶችን ኢንቨስትመንት የመውረስ ጉዳይ አስመልክቶ በኢንቨስትመንት አመንጪና ተቀባይ አገሮች መካከል የነበረው የተካረረ ጭቅጭቅ እንዴት መፍትሄ እንደሚያገኝ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በዚህ መልኩ የሚከሰቱ አለመግባባቶች እንዴት ሊፈቱ እንደሚችሉ መንገዶችን መፈለግ ጀመረ ...*[28]

**የተገባ አስተውሎት እጥረት ያለባቸው** (paucity of intentionality) **ኢትዮጵያ የፈረመቻቸው የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ስምምነቶች መኖር ይህን የሎወንፌልድን አመለካከት እውነት ወይም ውሸት አያደርገውም። ምንም እንኳን በግልፅ የሚነገር አሳማኝ ምክንያት ባይገኝለትም፥ እ.አ.አ.** በ2010 **ገደማ ሁሉም የተፈረሙ የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በድንገት እንዳይፀድቁ መደረጉ የተገባ አስተውሎት እጥረት ጉዳይ ስለመሆኑ የሚያጠናክር ነው። ከዚህ ቀደም ብሎ እንደተገለፀው ህንድ የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ያፀደቀችበትና አፈፃፀማቸውን የተከታተለችበት መንገድ ቻይና ከተከተለችው እጅጉን የወረደ በመሆኑ ለከፋ አሉታዊ ሁኔታዎች ዳርጓታል።** [29]

## 2.2. በስራ ላይ ያለው የኢንቨስትመንት አዋጅ

**አሁን በስራ ላይ ያለው የኢትዮጵያ የኢንቨስትመንት ሕግ መጋቢት** 24 **ቀን** 2012 **ዓ.ም. የወጣው የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር** 1180/2012 **እና የኢንቨስትመንት ደንብ ቁጥር**

[28] ANDREAS LOWENFELD, INTERNATIONAL ECONOMIC LAW 536 (2nd ed. 2008).

[29] Won Kidane, *China's* and *India's* Investment Treaty Experiences, ***ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁ. 13 የተጠቀሰ።***

474/2020 ነው።[30] ይህ ደግሞ በንጉሰ ነገስቱ ዘመን በ1948ቱ ሕገ መንግስት[31] ስር ፀድቆ ከነበረው የ1955ቱ የኢንቨስትመንት አዋጅ[32] የተጀመረውና በየደረጃው እየዘመነ የመጣው

[30] የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 1180/2012። የተሻሻለውን የኢንቨስትመንት አዋጅ የቀድሞመውን የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁ. 769/2004 እና የኢትዮጵያ መንግስት የኢንቨስትመንት ቦርድና የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 313/2006 ተክቷል። የአዋጅ ቁ. 1180/2012፣ አንቀጽ 56ን ይመልከቱ። እንዲሁም የኢትዮጵያ የኢንቨስትመንት ደንብ ቁ.474/2012ን ይመልከቱ። ይህ ደንብ ከዚህ በፊት የነበረውን የኢንቨስትመንት ማበረታቻ እና ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች የተከለሉ የሥራ መስኮች ደንብ ቁ. 270/2005ን በከፊል ሽሯል።

[31] የኢትዮጵያ የተሻሻለው የ1955 ሕገ መንግስት https://archive.org/stream/TheEthiopianConstitution/EC_djvu.txt

[32] Decree No. 51 of 1963፥ ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁ. 16 የተጠቀሰ። ዘመናዊ የኢንቨስትመንት ጥበቃ እሳቤዎች እ.ኤ.አ. በ1951 በኢትዮጵያ እና በአሜሪካ መካከል በተደረገው የወዳጅነት እና የንግድ ስምምነት ውስጥ ተንፀባርቀዋል። ሰነዱን በዚህ ድረ-ገፅ ማግኘት ይቻላል። http://tcc.export.gov/Trade_Agreements/All_Trade_Agreements/exp_002815.asp. ይህ ስምምነት በ1994 ተሻሽሏል። ሰነዱን ለማየት ይህን ድረ-ገፅ ይመልከቱ፡- https://www.trade.gov/knowledge-product/ethiopia-trade-agreements. የስምምነቱ አንቀጽ 8 የሚከተለውን ደንግጓል፡-

1. Each High Contracting Party shall at all times accord fair and equitable treatment to nationals and companies of the other High Contracting Party, and to their property and enterprises; shall refrain from applying unreasonable or discriminatory measures that would impair their legally acquired rights and interests; and shall assure that their lawful contractual rights are afforded effective means of enforcement, in conformity with the applicable laws.

(እያንዳንዳቸው ተዋዋይ ወገኖች ሁልጊዜም የሌላውን ተዋዋይ አገር ዜጎች ወይም ኩባንያዎችን እንዲሁም ንብረታቸውንና የቢዝነስ ስራዎቻቸውን በተመለከተ ፍትሃዊና ርትአዊ በሆነ መልኩ ማስተናገድ አለባቸው፤ በሕግ አግባብ ያገኙትን መብትም ሆነ ጥቅም የሚነካ ምክንያታዊ ያልሆኑ ወይም አድሏዊ የሆኑ እርምጃዎችን ከመውሰድ መታወቀብ አለባቸው፤ አግባብ ባለው ሕግመሰረት በተደረገ ውል መሰረት ያገኟቸው መብቶች ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲፈፀምላቸው ማድረግ አለባቸው።)

2. Property of nationals and companies of either High Contracting Party, including interests in property, shall receive the most constant protection and security within the territories of the other High Contracting Party. Such property shall not be taken except for a public purpose, nor shall it be taken without the prompt payment of just and effective compensation.

(የማናቸውም ተዋዋይ ሀገር ዜጎች ወይም ኩባንያዎች ያላቸው ንብረትና በንብረት ላይ ያሉ ጥቅሞች በሌላኛው ተዋዋይ ወገን ግዛት ወጥ የሆነ ዋስትናና ጥበቃ ሊደረግላቸው ይገባል። ለህዝብ ጥቅም ካልሆነ ንብረታቸው ሊወሰድ አይገባም፤ የሚወሰድም ከሆነ በአፋጣኝ የሚከፈል ፍትሃዊና አጥጋቢ ካሳ ሳይከፈል ሊወሰዱ አይገባም።)

አንዱ የሌላውን ተዋዋይ አገር ዜጋ ከመቀበል ጋር ተዛማጅነት ያለው ሌላ ጉዳይ MFN (Most Favoured Nation) አንቀፅ ነው። አንቀጽ 4 የሚከተለው ይላል፡-

**የኢትዮጵያ የሕግ ማመንጨት ጥረት ቀጣይ ሂደት ውጤት ነው። አዋጅ ቁጥር** 1180/2012 **ቀዳሚውን የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር** 769/2004 **(እንደተሻሻለው) እና የኢትዮጵያን ኢንቨስትመንት ቦርድ እና የኢንቨስትመንት ኮሚሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር** 313/2006 **የተካ ነው።** [33]

**ከአዋጁ ስምንት የመግቢያ ዓረፍተ ነገሮች ሁለቱ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ማንሳታቸው አዋጁ የድንበር ተሻጋሪ ኢንቨስትመንት ጉዳዮችን የሚገዙ አንቀፆችን እንደሚይዝ ፍንጭ ሰጭዎች ናቸው።** [34] **አዋጁ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ ባለሀብቶች ላይ ተፈፃሚ ነው። እንዲያውም ባለሀብት የሚለውን ቃል ሲተረጉመው እንዲህ ይላል፤ "'ባለሀብት' ማለት ኢትዮጵያ ውስጥ ካፒታል ሥራ ላይ ያዋለ የአገር ውስጥ ወይም የውጭ ባለሀብት ነው።"**[35]

---

1. Nationals of either High Contracting Party shall be permitted, subject to immigration laws and regulations, to enter the territories of the other High Contracting Party and to reside therein for the purpose of engaging in industry, carrying on international trade, or pursuing studies, upon terms no less favorable than those accorded to nationals of any third country.

*(የኢሚግሬሽን ሕጎችና ደንቦች በሚፈቅዱት መሰረት እና ለሌሎች አገራት ዜጎች ከሚደረገው የአተያት ደንቦች ባላነሰ ሁኔታ የአንዱ ተዋዋይ ሀገር ዜጎች ወደሌላኛው ተዋዋይ ሀገር በመግባትና በመኖር በኢንዱስትሪ፣ በዓለም አቀፍ ንግድ ወይም በትምህርት እንዲሳተፍ ይፈቀድላቸዋል።)*

[33] **አዋጅ ቁ.** 1180/2012 **አንቀጽ** 56**ን ይመልከቱ። ከ**2004**ቱ አዋጅ በፊት የነበሩት ሕጎች የሚከተሉትን ያካትታሉ (ሁሉም እ.አ.አ.)፡-**
**የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር** 37/1996**፤ የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር** 280/2002**፤ አዋጅ ቁጥር** 116/1998**፤ አዋጅ ቁጥር** 168/1999**፤ አዋጅ ቁጥር** 375/2003**፤ አዋጅ ቁጥር** 103/1998 **(የካፒታል ዕቃዎች ኪራይ ንግድ አዋጅ) እና አዋጅ ቁጥር** 543/2007 **(የተሻሻለው የወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ዕቅድ ማቋቋሚያ አዋጅ)፤ የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር** 769/2012**፤ የኢንቨስትመንት ደንብ ቁጥር** 270/2012 **እንዲሁም የማዕድን ማውጣት አዋጅ ቁጥር** 678/2010 **እና የነዳጅ ስራዎች አዋጅ ቁጥር** 295/1986**። ዋናው ተከታይ ህግ የኢንዱስትሪ ፓርኮች አዋጅ ቁጥር** 886/2015 **ነው። ከ**1974 **እስከ** 1991 **በነበረው የወታደራዊ አገዛዝ ወቅት የሕግ አውጭ ተግባራትን በተመለከተ ይህን ሰነድ ይመልከቱ፡-** Library of Congress, Ethiopia: A Country Study (1991), at pp. 187-190.

[34] **የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር** 1180/2012 **መግቢያ ይመልከቱ።**

*ወደ አገር ውስጥ የሚገባውን የውጭ ባለሀብቶች ኢንቨስትመንት መጠን እና የተሳትፎ መስክ በማስፋት የዕውቀት፣ የክህሎት፣ እና የቴክኖሎጂ ሽግግር እና ስርጸትን ማፋጠን ተገቢ መሆኑን በመገንዘብ፤ በውጭ እና የአገር ውስጥ ኢንቨስትመንቶች መካከል ትስስርን ማስፋት፣ የኢንቨስትመንት ክልላዊ ስርጭትን ማሻሻል፣ እንዲሁም የውጭ ካፒታል በመጠቀም የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን ተወዳዳሪነት ማሳደግ አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ፤*

[35] **የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር** 1180/2012**፣ አንቀጽ** 2(4)**።**

"የውጭ ባለሀብት" የሚለው ደግሞ እንደሚከተለው ተተርጉሟል፡-

> *የውጭ ካፒታል ወደ ኢትዮጵያ በማስገባት ሥራ ላይ ያዋለ፤ ሀ) የውጭ አገር ዜጋ፤ ለ) የውጭ አገር ዜጋ በባለቤትነት የተሳተፈበት ድርጅት፤ ሐ) በማንኛውም ባለሀብት ውጭ አገር የተቋቋመ ድርጅት፤ መ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፯) ፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ) ወይም (ሐ) በተመለከቱት ማናቸውም ባለሀብቶች መካከል በጋራ የተቋቋመ ድርጅት፤ ወይም፤ ሠ) እንደ ውጭ ባለሀብት መቆጠር የፈለገ መደበኛ ነዋሪነቱ ውጭ አገር የሆነ ኢትዮጵያዊ ነው።*[36]

የኢንቨስትመንት አዋጁ ለአገር ውስጥ ባለሀብት ብቻ የተከለሉ የኢንቨስትመንት ዘርፎችን፥ ወይም ከውጭ ባለሀብት ጋር የሚሰሩ በቅንጅት የሚሰሩ ዘርፎች እንዳሉ ደንግጎ ዝርዝሩን ወደፊት ለሚወጣው ደንብ ይተወዋል።[37] ብዙም ሳይቆይ በቀጣይነት የወጣው ደንብም እነዚህን ዝርዝሮች ይዟል።[38]

ለድንበር ተሻጋሪ ጉዳዮች አግባብነት ያላቸው የአዋጁ ክፍሎች የኢንቨስትመንት ጥበቃንና አለመግባባቶችን ስለመፍታት የተደነገጉት ናቸው። የኢንቨስትመንት ጥበቃን አስመልክቶ በሌሎች የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ውስጥ ከተጠቀሱት ጥበቃዎች ጋር ተቀራራቢነት ያለው አንቀፅ አንድ ብቻ ሲሆን፥ እርሱም ስለ ኢንቨስትመንት ዋስትና የሚደነግገው አንቀፅ ነው። አብዛኞቹ የኢንቨስመንት ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ይህን ጥበቃ የሚደነግጉት በከልካይነት አቀራረፅ እንዲህ በማለት ነው፥ "ማንኛውም ተዋዋይ ወገን [ኢንቨስትመንትን] ሊወስድ (ሊወርስ) አይችልም። ሊወስድ (ሊወርስ) የሚችለው ግን …። " የኢትዮጵያው ሕግ ደግሞ ጥበቃውን በማፅናት ረገድ በተመሳሳዩ ሲደነግግ፥ የአንቀፁን አቀራረፅ ግን እንደሚከተለው በፈቃጅነት ይዘቱ አስቀምጦታል፥ "መንግሥት በዚህ አዋጅ መሠረት የሚካሄድ ማንኛውንም ኢንቨስትመንት ለሕዝብ ጥቅም፣ በሕግ አግባብ፣ እና ያለመድልዎ ሊወስድ ይችላል።"[39] በመቀጠልም "ማንኛውም ኢንቨስትመንት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚወሰድ ከሆነ በወቅቱ የገበያ ዋጋ ተመጣጣኝ ካሣ በቅድሚያ መከፈል አለበት" በማለት ደንግጓል።[40]

---

[36] *ዝኒ ከማሁ*፣ አንቀጽ 2 (6)።

[37] *ዝኒ ከማሁ*፣ አንቀጽ 6።

[38] *ዝኒ ከማሁ*፣ አንቀጽ 3 እስከ 6።

[39] *ዝኒ ከማሁ*፣ አንቀጽ19(1)።

[40] *ዝኒ ከማሁ*፣ አንቀጽ 19(2)።

**ኢንቨስትመንትን የመውረስ (የመውሰድ) መርህ አከራካሪና አጨቃጫቂ የሆነውን ያህል ሌሎች በአወዛጋቢነት የተሞሉ የዓለም አቀፍ ሕግ መርሆዎች ጥቂት ናቸው። ከላይ የተመለከትነው አንቀፅ ምንም እንኳን በቀጥታ ቃል በቃል ባይወስደውም በስፋት ተቀባይነትን ካገኘውና ፅንሰሀሳቡን ባመነጨው በቀድሞው የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በሚ/ር ኮርዴል ሁል[41] ስም ከሚጠራው "የሁል ፅንሰሃሳብ" ጋር ተቀራራቢነት አለው። "የካልቮ ዶክትሪን"[42] በመባል ከሚታወቀው ፅንሰሃሳብ ጋር ያለውን ስር የሰደደ ተቃርኖ**

---

[41] **የኮርዴል ሁል በጣም ታዋቂው መግለጫ የሚከተለው ነው።**

> The taking of property without compensation is not expropriation. It is confiscation. It is no less confiscation because there may be an expressed intent to pay at some time in the future. If it were permissible for a government to take the private property of citizens of other countries and pay for it as and when, in the judgment of that government, its economic circumstances and its local legislation may perhaps permit, the safeguards which the constitutions of most countries and established international law have sought to provide would be illusory. Governments would be free to take property far beyond their ability or willingness to pay, and the owners thereof would be without recourse. We cannot question the right of a foreign government to treat its own nationals in this fashion if it so desires. This is a matter of domestic concern. But we cannot admit that a foreign government may take the property of American nationals in disregard of the rule of compensation under international law. Nor can we admit that any government unilaterally and through its municipal legislation can, as in this instant case, nullify this universally accepted principle of international law, based as it is on reason, equality and justice.
>
> **(ያለ ካሳ ንብረትን መውሰድ በህግ መውሰድ አይደለም። መቀማት ነው። ለወደፊቱ ለመክፈል የተገለጸ ዓላማ ሊኖር ስለሚችል ብቻ ከመቀማት አይተናነስም። መንግሥት የውጪ ሀገር ዜጎችን ንብረት እንዲወስድ፤ ካሳ የሚከፍለውም የሀገሪቷን ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ እና ሀገረኛ ሕጎችን በመመርኮዝ ከሆነ፤ በብዙ ሀገራት ሕገ-መንግሥቶችና በዓለም አቀፍ ሕግጋት የተቋቋሙት የንብረት መብት ጥበቃዎች ቅዠት ይሆናሉ። መንግስታት ለመክፈል ከአቅማቸው ወይም ከፍላጎታቸው በላይ የሆነ ንብረት ለመውሰድ ነፃ ይሆናሉ። ይህም ባለቤቶቹን ያለመፍተሄ ያስቀራቸዋል። የውጭ መንግስት የራሱን ዜጎች በዚህ መልኩ የማስተናገድ መብቱን ልንቃወም አንችልም፤ ምክንያቱም ይህ የሀገር ውስጥ ጉዳይ ነው። አንድ የውጭ መንግስት የአሜሪካ ዜጎችን ንብረት በአለም አቀፍ ሕግ ስር የተቀመጠውን የካሳ ሕግ ችላ በማለት መውሰዱን መቀበል አንችልም። ከሱም አልፎ መንግሥት በአንድ ጎን ብቻ ሁኖ ይህን በምክንያታዊነት፤ በእኩልነትና በፍትህ ላይ የተመሰረተን፣ ተቀባይነት ያለውን፣ የዓለም አቀፍ ሕግ መርህ በሀገሪቷ ሕግ መሻር አግባብነት ያለው አይደለም)**
>
> U.S. Secretary of State communications to Mexican Ambassador to the United States, Jul. 21, 1938 as quoted in Lowenfeld, ***ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁ. 28*** **የተጠቀሰ፥** ***ገፅ*** 474-475.

[42] The essence of the Calvo doctrine is that

በማቻቻል "የሁል ፅንሰሀሳብ" ኢንቨስትመንትን የሚወስድ (የሚወርስ) አካል የሚከፍለው ካሳ "ወዲያውኑ (prompt)፣ በቂ (adequate) እና ውጤታማ (effective)" መሆን አለበት የሚሉ በስፋት ተቀባይነትን ያገኙ ግልፅ መርሆዎችን አስተዋውቋል።[43]

---

> [a]liens who establish themselves in a country have the same right to protection as nationals, but they ought not to lay claim to a protection more extended. If they suffer any wrong, they ought to count on the government of the country prosecuting the delinquents, and not claim from the state to which the authors of the violence belong any pecuniary indemnity … The rule that in more than one case it has been attempted to impose on American states is that foreigners merit regard and privilege more marked and extended than those accorded even to the nationals of the country where they reside. The principle is intrinsically contrary to the law of equality of nations.
>
> **(የካልቮ አስተምህሮ ዋና ይዘት የሚከተለው ነው፡-**
> **በአንድ ሀገር ውስጥ እራሳቸውን ያቋቋሙ የውጪ ዜጎች እንደ ዜጎች ተመሳሳይ ጥበቃ የማግኘት መብት አላቸው እንጅ ከዚያ ለላቀ ከለላ መጠየቅ የለባቸውም። በደል ቢደርስባቸው የሀገሪቱ መንግስት ጥፋተኞችን ለፍርድ እንደሚያቀርብ ሊያምኑ ይገባል እንጂ የገንዘብ ካሳ ጥያቄ ሊያነሱ አይገባም። … ከአንድ በላይ በሆኑ በአሜሪካ ግዛቶች ላይ ለመጣል የተሞከረው ደንብ፣ ለሀገሪቷ ዜጎች እንኳን ከተሰጣቸው የበለጠ ክብር እና ልዩ መብት ለውጭ ዜጎች የሚሰጥ ነው። ይህ መርህ ደግሞ በመሠረታዊነት የሃገራት ከእኩልነት መርሕ ጋር የሚጋጭ ነው።)**
>
> Donald R. Shea, "The Calvo Clause" (1955), 17–19, as quoted in Lowenfeld, ***ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁ.*** 28 የተጠቀሰ፥ ገፅ 473።

[43] **ስለዚህ መርህ የበለጠ ማብራሪያ፡-** Frank G. Dawson & Burns H. Weston, 'Prompt, Adequate and *Effective'*: A Universal Standard of Compensation? 30 FORDHAM LAW REVIEW 727 (1962). **የካሳ ክፍያን በተመለከተ በተደጋጋሚ የሚጠቀሰው የአለም አቀፍ ህግ መርህ** PCIJ (Permanent Court of International Justice) **በ** Chorzow Factory **ጉዳይ ላይ የሰጠው መግለጫ ነው፡-**

> The essential principle contained in the actual notion of an illegal act—a principle which seems to be established by international practice and in particular by the decision of international arbitral tribunals—is that reparation must, as far as possible, wipe out all the consequences of the illegal act and reestablish the situation which would, in all probability, have existed if that act had not been committed. Restitution in kind, or, if this is not possible, payment of a sum corresponding to the value which a restitution in kind would bear; ...
>
> **(እንደ አለም አቀፍ አሰራር እና በተለይም በዓለም አቀፍ የግልግል ፍርድ ቤቶች ውሳኔ፣ የህገ-ወጥ ድርጊት ጽንሰ-ሀሳብ ካሳ በተቻለ መጠን የሕገ-ወጥ ድርጊቱን ውጤቶች በሙሉ ማጥፋት እንዲሁም ድርጊቱ ባይፈፀም ኖሮ ሊሆን ወደሚችለው ሁኔታ መመለስ እንዳለበት የሚያትት መሠረታዊ መርህን የያዘ ነው። በአይነት መመለስ፣ ወይም ይህ የማይቻል ከሆነ፣ በአይነት ቢመለስ ሊያወጣ ከሚችለው ዋጋ ጋር ተቀራራቢ ክፍያ መክፈል።)**

Permanent Court of International Justice, Case Concerning German Interests in Upper Silesia, P.C.I.J. SERIES A, Nos. 7, 9, 17, 19 (1926–1929) at 47.

አንድ የኢንቨስትመንት አዋጅ ይዘት በስራ ላይ ካሉት የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ጥበቃ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ለኢንቨስትመንት ከሰጡት ጥበቃ ጋር መሰረታዊ ልዩነት ካለውና ግጭት የሚከሰት ከሆነ፥ አለመግባባቱን ለመዳኘት የሚመረጠው የግልግል ዳኝነት ጉባዔ (ፍርድ ቤት) ወይም ሌላ የፍትሕ መድረክ ገዢው ሕግ የሚመርጠውን የሕጎች ቅደምተከተል ከግምት እንዲያስገባ ግድ ይሉታል። የኢንቨስትመንት ክርክሮች በመሰረቱ በቅድሚያ የሚያተኩሩት ኢንቨስትመንቱ ተወርሷል (ተወስዷል) ወይስ አልተወሰደም የሚለው ጉዳይ ላይ ነው። ኢንቨስትመንቱ ተወርሶ (ተወስዶ) ከሆነ ደግሞ በቀጣይነት ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ የተከፈለው ካሳ በቂና ወዲያውኑ መሆኑ ላይ ነው። የወቅቱን የገበያ ዋጋ የመወሰን ጉዳይ አንድ ኢንቨስትመንት ሲወሰድ (ሲወረስ) ኢንቨስትመንቱ በተወረሰበት ወቅት ወይም እንደሚወሰድ የወሳኙ ዝንባሌ ገሃድ በተደረገበት ወቅት ያለውን የወቅቱን የገበያ ዋጋ መወሰን እጅጉን አስቸጋሪ በመሆኑ ዳኞች ይህንን ተግባር የሚያከናውኑት የተመሰከረላቸው ዋጋ ገማቾችን የሙያ እገዛ በመጠቀም ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ አዲሱ የኢንቨስትመንት አዋጅ “በወቅቱ ባለው የገበያ ዋጋ” (prevailing market value) በማለት የደነገገው መርህ በንፅፅር ሲታይ የተሻለ መሰረትን የጣለ ቢሆንም፤ ተከራካሪ ወገኖች ግን ዋጋን አስመልክቶ የሚሰላበትን ወቅትና ተዛማጅ ጉዳዮችን በማንሳት ልዩነት ሊፈጥሩ እንደሚችሉ መገመት አዳጋች አይሆንም። ይበልጡን ግን ችግር የሚሆነው ገዢው የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ጥበቃ ዓለም አቀፍ ስምምነት ስለ ዋጋ ግምት ከዚህ የተለየን መርህ ካስቀመጠ ነው። እንዲህ ያለ ዓለም አቀፍ ስምምነት ካለ ግን፥ ስምምነቱ የቅድሚያ መርህን (priority or preemption) ስርዓት በራሱ ደንግጎ ካልያዘ ብሔራዊ ሕጉ ያስቀመጠውን መስፈርት ተፈፃሚ የሚያደርግ ውጫዊ መመዘኛን (ስታንዳርድን) ያስተናግዳል።

ይህ አስተሳሰብ ደግሞ ምናልባትም ዋነኛ ወደ ሆነው አለመግባባቶችን ስለመፍታት ርዕሰ-ጉዳይ ይወስደናል።

## 3. የኢትዮጵያ ድንበር ተሻጋሪ ያለመግባባትን መፍቻ ስርዓት

ሕጉ ሁለት ስፊ እንድምታ ያላቸውን ድንበር ተሻጋሪ አለመግባባቶችን የተመለከቱ ጉዳዮች በማንሳቱ ሊወደስ ይገባዋል። እነዚህም ኢንቨስትመንትና ንግድን የተመለከቱ አለመግባባቶች ናቸው።

## 3.1. የኢንቨስትመንት አለመግባባቶች አፈታት

የኢንቨስትመንት አለመግባባቶችን የመፍቻ መንገዶችን አስመልክቶ በኢትዮጵያ አሁን በስራ ላይ ያሉት ድንጋጌዎች የሚገኙት በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 1180/2012 እና በስራ ላይ ባሉት 21 የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ውስጥ ነው።

የኢንቨስትመንት አዋጁ የኢንቨስትመንት አለመግባባት አፈታትን የተመለከተ ራሱን የቻለ ንዑስ ክፍል አለው። የቅሬታ ማቅረቢያ ስርዓትንም አካትቷል።[44] የአቤቱታ ስርዓቱ የኢንቨስትመንት ፍቃድን ስላለመስጠትና ስለመሰረዝ እንዲሁም የኢንአቨስትመንት ማበረታቻዎችን ስለመከልከል ወ.ዘ.ተ ታሳቢ አድርጎ የያዘ ነው።[45] በሀገር ውስጥ ሕጎችም ሆነ በሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የተሰጡ ቢሆንም እንደዚህ ያሉ አቤቱታዎች በባለሀብት መብቶች ላይ ተፅእኖን የሚያሳርፉ ናቸው።

መሰረታዊ የሆነው መርህ በአዋጁ አንቀፅ 25(1) ላይ እንደሚከተለው ተደንግጓል፥ *"፩/ ማንኛውም ባለሀብት ከኢንቨስትመንቱ ጋር የተያያዘ ቅሬታ ካለው አግባብ ላለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው።"* የአዋጁ የትርጉም ክፍል ደግሞ *"አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት"* የሚለውን ሲተረጉም *"ኮሚሽኑ፣ ከኮሚሽኑ በውክልና ሥልጣን የተሰጠው የፌደራል መንግሥት አካል፣ ወይም የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለመስጠት ወይም ኢንቨስትመንት ለማስተዳደር ሥልጣን የተሰጠው የክልል መስተዳድር አካል ነው፤"*[46] ይላል። ኮሚሽኑ የቀረበለትን አቤቱታ ተቀብሎ ውሳኔ እንዲሰጥ የሚጠበቅበት ጊዜም ገደብ ተጥሎበታል።[47] የአዋጁ የተወሰኑ አንቀፆች በባለሀብትና በመንግስት ተቋማት መካከል ለሚነሱ አለመግባባቶች ከፍርድ ቤት ወይም ከግልግል ዳኝነት በመለስ በሰላማዊ መንገድ የሚፈታበትን አካሄድ በማካተት የኢንቨስትመንት ኮሚሽኑ የአለመግባባቶችን መፍቻ የውሳኔ ሀሳቦችን ማቅረብ እንደሚችል ይደነግጋሉ። ይህን አስመልክቶ በአዋጁ የተመለከተው አንቀፅ እንዲህ በማለት ይደነግጋል፦

> *፩/ ማንኛውም ባለሀብት በዚህ አዋጅ መሠረት የሚካሄድ ኢንቨስትመንትን አስመልክቶ በፌደራል መንግሥት አስፈጻሚ አካል የተላለፈን በኢንቨስትመንቱ ላይ ጉልህ ተጽዕኖ የሚያደርስ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔን የተመለከተ አቤቱታ ለኮሚሽኑ የማቅረብ መብት አለው።*

---

[44] የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 1180/2012 አንቀጽ 25-27 ይመልከቱ።

[45] *ዝኒ ከማሁ።*

[46] *ዝኒ ከማሁ፣* አንቀጽ 2(16)።

[47] *ዝኒ ከማሁ፣* አንቀጽ 26-27።

*፪/ የማናቸውም የፌደራል መንግሥት አስፈጻሚ አካል የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ የጽሑፍ ቅጂ በሰባት (፯) የሥራ ቀናት ውስጥ ለባለሀብቱ ይሰጠዋል።*

*፫/ በፌደራል መንግሥት አስፈጻሚ አካል በተሰጠ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለኮሚሽኑ የሚቀርብ ማንኛውም አቤቱታ ባለሀብቱ ውሳኔው መሰጠቱን ካወቀበት ቀን ጀምሮ በሰላሳ (፴) የሥራ ቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት።*

*፬/ ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት የቀረበ አቤቱታ መፍትሔ እንዲያገኝ አቤቱታ ከቀረበበት የመንግሥት አካል ጋር በመነጋገር አቤቱታው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ በሰላሳ (፴) ቀናት ውስጥ የመፍትሔ ሀሳብ በጽሑፍ ያቀርባል።*[48]

የኮሚሽኑ ውሳኔ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ወይም ጠቅላይ ሚኒስትሩ የወከለው ሰው በሚመራው ቦርድ ላይ ይግባኝ ሊቀርብበት ይችላል።[49] በአዲሱ የፌደራል የአስተዳደር ስነስርዓት አዋጅ መሰረት ግን የቦርዱ ውሳኔ በፍርድ ቤት ሊከለስ እንደሚችል ይገመታል።[50]

በማይገርም መልኩ የቦርዱ ውሳኔ ይግባኝ የማይባልበት ነው። *"የቦርዱ ውሳኔ የሚመለከተው ማንኛውም የፌደራል መንግሥት አካል ውሳኔውን የማክበር እና በውሳኔው መሠረት የመፈጸም ግዴታ አለበት።"*[51]

ከአስተዳደራዊ መንገዶቹ በተጨማሪ አዋጁ ዓለም አቀፋዊውን የባለሀብትና የመንግስት የአለመግባባት መፍቻ ስርዓትን (Investor State Dispute Settlement-"ISDS") ታሳቢ አድርጓል። ይህን አስመልክቶም የአዋጁ የተወሰኑ አንቀፆች እንዲህ በማለት ይደነግጋሉ፤

*፩/ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን በተሰጠው አካል ፍትሕ የማግኘት መብትን ሳይቃረን፣ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚካሄድ ኢንቨስትመንትን በተመለከተ በባለሀብት እና*

---

[48] *ዝኒ ከማሁ፣* አንቀጽ 27 (1-4)።

[49] *ዝኒ ከማሁ፣* አንቀጽ 27(6)። "6/ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (4) መሠረት ያቀረበውን የመፍትሔ ሀሳብ በመቃወም፣ ወይም የተሰጠው የመፍትሔ ሀሳብ አቤቱታ በቀረበበት የመንግሥት አካል ተቀባይነት ያላገኘ እንደሆነ ባለሀብቱ ለቦርዱ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል።" የቦርዱን ስብጥር ለማየት አንቀጽ 30ን ይመልከቱ።

[50] *ዝኒ ከማሁ፣* አንቀጽ 27(9)።

[51] የፌደራል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012፣ አንቀጽ 48። "የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፰ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፡- 1/ ማንኛውም ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው የአስተዳደር መመሪያ በፍርድ ቤት እንዲከለስ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፤ 2/ ማንኛውም በአስተዳደር ውሳኔ ጥቅሙ የተነካበት ሰው ውሳኔው በፍርድ ቤት እንዲከለስ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል።"

*በመንግሥት መካከል የሚነሳ ማንኛውም አለመግባባት በውይይት ወይም በድርድር ይፈታል።*

*፪/ የፌደራል መንግሥት የውጭ ኢንቨስትመንትን በተመለከተ የሚነሱ የኢንቨስትመንት አለመግባባቶች በግልግል ዳኝነት እንዲፈቱ ሊስማማ ይችላል።*

*፫/ የውጭ ባለሀብት የኢንቨስትመንት አለመግባባትን በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል ወይም ለግልግል ዳኝነት ለማቅረብ ከመረጠ ምርጫው የመጨረሻ እና ሌላኛውን ከመጠቀም የሚያግድ ይሆናል።*[52]

**ንዑስ አንቀፅ 3 በኢንቨስትመንት ሕግ "ባለሹካ መንገድ"** ("fork-in-the-road") **በመባል የሚታወቀውን አንድ ባለሀብት አንድን የኢንቨስትመንት ክስ በተለያዩ የፍትሕ መድረኮች ሊያቀርብ አይችልም የሚለውን መርህ ያስተዋወቀ ነው። ይሁን እንጂ የዚህን ንዑስ አንቀፅ አተረጓጎም አስመልክቶ ጥያቄን የሚያስነሳ ጉዳይ ሊከሰት ይችላል። ይኸውም ቦርዱ የሰጠውን ውሳኔ ፍርድ ቤት በይግባኝ እንዲያየው ማድረግ ከ"ባለሹካ መንገድ" መርህ አንፃር የፍትሕ መድረክ ምርጫ ተደርጎ ሊተረጎም ይችላል የሚልን ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል ወይ የሚል ነው። የሂደቱ ውጤትም "የፍትህ ክልከላ"** (Denial of justice")[53] **ነው በሚል በአንዳንድ የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ስምምነቶች መሰረታዊ የሕግ ጥሰት ናቸው ተብለው የተደነገጉትን የ"ፍትሃዊና ርትዓዊ አገልግሎት"** (fair and equitable treatment—"FET") **መርህን ጥሰት ጉዳይ ሊያስነሳ ይችላል።**[54] **ይህ ዓይነቱ ከስር ያሉ የፍትሕ አማራጮችን**

---

[52] **የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር** 1180/2012፥ **አንቀጽ** 28።

[53] **ጃን ፖልሰን** እንዳስቀመጠው፡- (i) the denial of justice is essentially procedural in nature; (ii) it does not require the State to create a perfect system of justice but rather a system of justice that could correct serious errors; and, more importantly, (iii) the denial of justice requires the exhaustion of local remedies and the showing of a system failure. [(1) **ፍትህ መንፈግ በተፈጥሮው የሥነ-ስረዓት መዛባት ነው፤** (2) **መንግሥት ፍፁም የሆነ የፍትሕ ሥርዓት እንዲፈጥር ሳይሆን ከባድ ስህተቶችን የሚያስተካክል የፍትሕ ሥርዓት እንዲፈጥር ነው የሚያስፈልገው፤ በይበልጥ ደግሞ፥** (3) **የፍትህ መነፈግ በአንድ ሀገር ውስጥ የመፍትሄዎችን ማሟጠጥ እና የስርዓት ውድቀትን ያሳያል።**] Jan Paulsson, DENIAL OF JUSTICE IN INTERNATIONAL LAW, (2005) pp. 7-8.

[54] **በ** FET **እና በፍትህ መነፈግ መካከል ያለው ግንኙነት በደንብ የተረጋገጠ ነው። ለምሳሌ፥ የካናዳ-አውሮፓ ህብረት አጠቃላይ የኢኮኖሚ እና የንግድ ስምምነት አንቀጽ** 8.10 **የሚከተሉትን ያስቀምጣል፡-**

1. Each Party shall accord in its territory to covered investments of the other Party and to investors with respect to their covered investments fair and equitable treatment and full protection and security in accordance with paragraphs 2 through 7.
2. A Party breaches the obligation of fair and equitable treatment referenced in paragraph 1 if a measure or series of measures constitutes:

በየደረጃው የማጠናቀቅ ግዴታ ጉዳይ ፅንሰ ሃሳባዊ (theoretical) ብቻ አይደለም፤ እጅጉን ተደጋጋሚ በሆነ መልኩ የሚነሳ አከራካሪ የሆነ ጉዳይ እንጂ።

በተለያየ ደረጃም ቢሆን ኢትዮጵያ የተፈራረመቻቸው ሁሉም (21ዱም) የሁለትዮሽ ኢንቨስትመንት ስምምነቶች ዓለም አቀፋዊውን የባለሀብትና የመንግስት የአለመግባባት መፍቻ ስርዓትን ይዘዋል። በየአስርት ዓመቱ ከተፈረሙ የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ስምምነቶች ለአብነት የሚሆኑትን በመውሰድ የአለመግባባቶች መፍቻ አንቀፆቻቸው በየዘመኑ ያሳዩትን ዕድገት ለመተንተን ይረዳል።

በቅድሚያ ከመጀመሪያዎቹ ተርታ የሚመደበውንና የተሰረዘውን እ.አ.አ. በ1963 የተፈረመውን የኢትዮጵያንና የጀርመንን የሁለትዮሽ ስምምነት እንመልከት። የአለመግባባት መፍቻ አንቀፁ እንዲህ በማለት ይደነግጋል፤ "አንቀፅ 10(1) ከዚህ ስምምነት ጋር በተያያዘ የሚነሱ የትርጉምና የአተገባበር አለመግባባቶች ከተቻለ በሁለቱ ተዋዋይ ሀገሮች መንግስታት ይፈታሉ። (2) አለመግባባቶቹ በዚህ መንገድ ካልተፈቱ ጉዳዩ ከሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች ባንደኛው ወገን ጠያቂነት ለግልግል ዳኝነት ጉባዔ ይመራል።"[55] ከዚህ በመቀጠል ያሉት ንዑስ አንቀፆች የግልግል ዳኝነት ጉባዔውን አባላት ጥንቅርና ጉባዔው የሚመሰረትበትን ሁኔታ ይገልፃሉ። በስምምነቱ ውስጥ ያለ ያለመግባባት መፍቻ አንቀፅ ይህ ብቻ ሲሆን፤ ስምምነቱ በተፈረመበት እ.አ.አ. በ1964 ተዋዋይ ወገኖቹ በባለሀብትና በመንግስት መካከል ሊኖር ስለሚችል አለመግባባት የመፍቻን መንገድ አላካተተም ቢባል አግባብነት ያለው መደምደሚያ ነው።[56]

(a) *denial of justice in criminal, civil or administrative proceedings*;
(b) fundamental breach of due process, including a fundamental breach of transparency, in judicial and administrative proceedings;
(c) manifest arbitrariness;
(d) targeted discrimination on manifestly wrongful grounds, such as gender, race or religious belief;
(e) abusive treatment of investors, such as coercion, duress and harassment; or
(f) a breach of any further elements of the fair and equitable treatment obligation adopted by the Parties in accordance with paragraph 3 of this Article. (**አጽንዖት ተጨምሯል**) https://ec.europa.eu/trade/policy/in-focus/ceta/ceta-chapter-by-chapter/ ኢንቨስትመንትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በምዕራፍ 8 ተካተዋል።

[55] የ1964 ኢትዮ-ጀርን ስምምነት፥ *በግርጌ ማስታወሻ* ቁ. 17 የተጠቀሰ፥ አንቀጽ10።
[56] እንደ አጋጣሚ ሆኖ ይህ የኢትዮ-ጀርምን ስምምነት የተፈፀመው በ ICSID ረቂቅ ሰነድ ላይ ለመወያየት የአለም ባንክ የአፍሪካ የሕግ ምክክር መድረክ እ.ኤ.አ. በ1963 ከታህሳሥ 16 እስከ 20 በአዲስ አበባ

ከላይ እንደተገለፀው እ.አ.አ. በ1970ዎቹና በ1980ዎቹ ዓመታት ኢትዮጵያ የተፈራረመችው የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ስምምነት የለም። እ.አ.አ. በ1990ዎቹ ጥቂት እንቅስቃሴዎች የታዩ ሲሆን፤ ከነዚህም መካከል እ.አ.አ. በ1998 የተፈረመውና እ.አ.አ. በ2000 የፀደቀው የኢትዮጵያና የቻይናው የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ስምምነት ዋነኛው ነው። ይህ ስምምነት የቻይና የሁለትዮሽ ስምምነቶች የመጀመሪያ ትውልድ ስምምነት የያዙትንና ዓለም አቀፍ የግልግል ዳኝነትን ለጉዳት መጠን መወሰኛ ብቻ የሚገለገሉበትን አንቀፅ አካትቷል።

> 9(2). አለመግባባቱ በድርድር በስድስት ወራት ውስጥ እልባት ካላገኘ ከተዋዋይ ወገኖች አንደኛው ክሱን የኢንቨስትመንቱ ተቀባይ በሆነው ሀገር ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማቅረብ ይቻላል።... (3). ለኢንቨስትመንቱ መወሰድ (መወረስ) ሊከፈል የሚገባውን ካሳ አስመልክቶ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት በድረድር መፍታት ካልተቻለ፤ እ.አ.አ. በማርች 18 ቀን 1965 በዋሽንግተን ለፊርማ ክፍት የተደረገውን በመንግስታትና በሌሎች መንግስታት ዜጎች መካከል የሚነሳን የኢንቨንስትመንት አለመግባባቶች መፍቻ ዓለም አቀፍ ስምምነትን ሁለቱም ወገኖች እስካፀደቁ ድረስ በዚህ ስምምነት መሰረት በተቋቋመው የኢንቨስትመንት አለመግባባቶች ዓለም አቀፍ ማዕከል ጥላ ስር ለሚመሰረት ጊዜያዊ የግልግል ዳኝነት ጉባዔ ጉዳዩ ከተዋዋይ ወገኖች ባንደኛው ወገን ጠያቂነት ሊቀርብ ይችላል። ባለሀብቱ ግን በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 2 የተመለከተውን አማራጭ ለመከተል ከመረጠ፤ ይህ ንኡስ አንቀፅ ተፈፃሚ አይሆንም።[57]

ይህ በግልፅ እንደሚታየው ኢትዮጵያ የተከተለችው የቻይናን አካሄድ ነው። ምንም እንኳ ቻይና ይህን አማራጭ የተከተለችው በወቅቱ የምዕራቡ ዓለም ኢንቨስትመንት ተቀባይ አገር

---

ከተካሄደው ስብሰባ ከአንድ አመት ገደማ በኋላ ነው። International Centre for Settlement of Investment Disputes (ICSID), The History of the ICSID Convention, ICSIDD.WORLDBANK.ORG, https://icsid.worldbank.org/resources/publications/the-history-of-the-icsid-convention [https://perma.cc/Q2E5-797P] (last visited Jul. 11, 2021). በእርግጥ፥ ከ1964ቱ የICSID ስምምነት በፊት ISDS በአለም አቀፍ ህግ የማይታወቅ ነበር። እንዲያውም አንድ ግለሰብ በሉዓላዊ ሀገር ላይ ክስ በሚመሰርትበት ጊዜ የመሰማት መብቱን ስለሚያስጠብቅለት ያልተለመደ ነገር ሆኖ ሊቆጠር ይችላል።

[57] Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the People's Republic of China Concerning the Encouragement and Reciprocal Protection of Investments, art. 9(2-3), Ethiopia-China, 1998 [ከዚህ በኋላ Ethiopia-China BIT እየተባለ የሚጠቀስ], https://investmentpolicy.unctad.org/international-investment-agreements/treaty-files/732/download [https://perma.cc/PB9M-VHT7]. https://investmentpolicy.unctad.org/international-investment-agreements/treaty-files/732/ [https:// perma. cc /PB9M-VHT7] ስለ ቻይና የተለያዩ የሁለትዮሽ ስምምነቶች የበለጠ ለማወቅ ይህን ፅሁፍ ይመልከቱ፡- NORAH GALLAGHER & WENHUA SHAN, CHINESE INVESTMENT TREATIES (2009).

በመሆኗ የኃላፊነትን ጉዳይ በመወሰን ረገድ በብሄራዊ ፍ/ቤቶቿ መታየቱ ነፃነቷን ያስጠበቀላት ተደርጎ ቢወሰድም፣ ቻይና የኢንቨስትመንት ላኪ አገር ወደመሆን ስታድግም ይህንኑ መርኋን አልለወጠችም። ለዚህ ምክንያቱ የአካሄድ ወጥነትን ማረጋገጥ፣ የመርህ ጉዳይ፣ ራስን የመቻል ጉዞ ወይም አስተዳደራዊ ችኮነት ስለመሆኑ በእርግጠኝነት ለመናገር ከባድ ነው። ለማንኛውም ይህ አንቀጽ በባለሀብትና በመንግስት መካከል የሚነሳን አለመግባባት አስመልክቶ ኢትዮጵያ በ1990ዎቹ የፈረመቻቸው የኢንቨስትመንት ጥበቃ ዓለምአቀፍ ስምምነቶች የተከተሉትን አካሄድ በመግለፅ ረገድ በምሳሌነት የሚጠቀስ ነው።

ሦስተኛው ናሙና እ.አ.አ. በ2000ዎቹ ከተፈረሙት ስምምነቶች መካከል የኢትዮጵያና የኔዘርላንድስ የኢንቨስትመንት ጥበቃ ዓለምአቀፍ ስምምነት ነው። ስምምነቱ በባለሀብቶችና በመንግስታት መካከል የሚነሱ አለመግባባቶችን መፍታት በተመለከተ ዝርዝርና ዘመናዊ ነው።

> 9(2). አለመግባባቱ በሰላም እንዲፈታ ከተከራካሪ ወገኖች አንደኛው በጠየቀ በስድስት ወራት ውስጥ ካልተጠናቀቀ ተከራካሪው ባለሀብት ጉዳዩን ወደሚቀጥሉት መድረኮች መውሰድ ይችላል፣ (ሀ) መዋዕለ ንዋዩ በፈሰሰበት አገር ወደሚገኝ ስልጣን ወዳለው የተዋዋይ ወገን ፍ/ቤት፣ ወይም (ለ) ተዋዋይ ወገኖች አፅድቀውት ከሆነ እ.አ.አ. በኦክቶበር 14 ቀን 1966 በፀደቀውና በሀገሮችና በተዋዋይ ሀገሮች ባለሃብቶች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶችን መፍቻ አለም አቀፍ ስምምነት መሠረት ወደተቋቋመው የኢንቨስትመንት አለመግባባቶች መፍቻ አለምአቀፍ ማዕከል፣ ወይም (ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2(ለ) እንደተመለከተው ከተዋዋይ ወገኖች አንደኛው የአለም አቀፍ ስምምነቱ አፅዳቂ ካልሆነ በኢንቨስትመንት አለመግባባቶች መፍቻ ዓለምአቀፍ ማዕከል ስር የማዕከሉ ጽ/ቤት የኢንቨስትመንት ክርክሩን ሂደት በሚያስተዳድርበት የተጨማሪ አገልግሎት መስጫ ስርዓት በሚገዛው ደንብ ወይም፥ (መ) በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የዓለም አቀፍ ንግድ ሕግ የግልግል ዳኝነት ደንብ መሠረት በሚቋቋመው ጊዜያዊ ዓለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት ተቋም (ፍ/ቤት)። (3) አለመግባባቱ ከመፈጠሩ በፊት በሌላኛው ተዋዋይ ወገን ዜጎች የበላይነት ይተዳደር የነበርና ያንደኛው ተዋዋይ ወገን የተፈጥሮ ሰው (ኩባንያ) ዜግነት ያለው፣ በሀገሮችና በተዋዋይ ሀገሮች ባለሀብቶች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች መፍቻ ዓለም አቀፍ ስምምነት አንቀጽ 25 ንዑስ አንቀጽ 2(ለ) መሰረት የአንደኛው ወገን ዜጋ ተደርጎ ይቆጠራል። (4) የግልግል ዳኝነቱ ውሳኔ የመጨረሻና ይግባኝ የማይባልበት ሲሆን በብሄራዊ ሕጉ መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል። (5) እያንዳንዱ የስምምነቱ ፈራሚ አባል የኢንቨስትመንት

አለመግባባቶች እንዲፈቱ ከላይ በተመለከቱት አንቀፆች (paragraphs) ውስጥ ለተሰጡ አማራጭ መድረኮች ለማቅረብ ተስማምቷል። [58]

ይህ ድንጋጌ ዓለም አቀፍ የግልግል ዳኝነትን ሂደት አስመልክቶ በቂ ዝርዝር ጉዳዮችን አሳይቷል። ኢዝራኤል ኬሚካል ሊሚትድ ኤል ኤል ሲ (አይ ሲ ኤል) የተሰኘው ኩባንያ በባለሀብትና በሀገር መካከል የሚካሄድን አለመግባባት አስመልክቶ እ.ኤ.አ. በ2017 ኢትዮጵያን የከሰሰው ይህንኑ አንቀጽ መሠረት አድርጎ ነው። የዚህ ክስ ዝርዝር ጉዳይ በሚስጥር እንዲያዝ ህግ ስለሚያስገድድ ለማብራራት ባይቻልም፣ ስለክሱ መኖር ግን በሄግ ኒዘርላንድስ የሚገኘው ቋሚው የግልግል ዳኝነት ፍ/ቤት በሪፖርቱ ይዞታል። [59]

በባለሀብትና በመንግስት መካከል የሚኖር አለመግባባት የሚፈታበትን መድረክ (በምህፃረ ቃሉ "አይ ኤስ ዲ ኤስ" በመባል የሚታወቀው) ፈፅሞ ካለመቀበል ወደ ከፊል ቅበላ ማለትም የጉዳት መጠንን በመወሰን ጉዳይ ላይ ብቻ የ"አይ ኤስ ዲ ኤስ"ን መድረክ ወደ መቀበል፣ ከዚያም ሙሉ በሙሉ የአይ ኤስ ዲ ኤስን መድረክ ወደመቀበል የተሸጋገረውና ለ40 ዓመታት ያህል የቆየው አካሄድ እ.ኤ.አ. በ2010 ላይ እንዲቆም የተደረገ ይመስላል፤ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በኢትዮጵያ የፀደቀ አንድም የሁለትዮሽ ዓለም አቀፍ የኢንቨስትመንት ስምምነት የለም። [60]

## 3.2. የዓለም አቀፍ ንግድ አለመግባባቶችን ስለመፍታት

እ.ኤ.አ. በፌብሩዋሪ 2020 የኢትዮጵያ ፓርላማ በውጭ ሀገር የተሰጠን የግልግል ዳኝነት የመቀበልና የማስፈፀም ዓለም አቀፍ ስምምነትን (በአጭር መጠሪያው "የኒውዮርክ

[58] Agreement on Encouragement and Reciprocal Protection of Investments between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Kingdom of the Netherlands, art. 9, Ethiopia-Netherlands, 2003 [**ከዚህ በኋላ** Ethiopia-Netherlands BIT **እየተባለ የሚጠቀስ**], https://investmentpolicy.unctad.org/international-investment-agreements/treaty-files/1172/download [https://perma.cc/9GYC-ZQBF].

[59] ስለ ጉዳዩ የተወሰነ መረጃ በዚህ ድረ-ገፅ ይገኛል፡- https://pca-cpa.org/en/cases/153/ [https://perma.cc/455R-BWS2] ላይ ይገኛል።

[60] በኢትዮጵያ የመፅደቅ ሁኔታን በተመለከተ፥ የኢትዮጵያ የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ስምምነቶች፥ *በግርጌ ማስታወሻ* ቁ.11 የተጠቀሰ ። ዘገባው እንደሚያሳየው በ2010 እና 2018 መካከል ቢያንስ አራት የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ስምምነቶች የተፈረሙ ቢሆንም ይኸን ጽሑፍ በፃፉንበት ጊዜ አንዳቸውም በኢትዮጵያ አልፀደቁም። እነዚህ የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ስምምነቶች ከብራዚል፣ ኳታር፣ የተባበሩት አረብ ኤሚሬቶች እና ሞሮኮ ጋር የተፈፀሙ ናቸው። *ዝኒ ከማሁ*።

**ኮንቬንሽን" በመባል የሚታወቀውን) አፀደቀ።[61] እ.አ.አ. በኦገስት 4 ቀን 2020 ኢትዮጵያ የኒውዮርክ ኮንቬንሽንን በመቀበል አባል ሀገር ሆነች።[62] እ.አ.አ. በኤፕሪል 2 ቀን 2021 ደግሞ ኢትዮጵያ "የግልግል ዳኝነትንና የዕርቅ አሠራር ሥርዓትን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ቁጥር 1237/2013" (ከዚህ በኋላ "የኢትዮጵያ የግልግል ዳኝነት አዋጅ" ወይም "የግልግል ዳኝነት አዋጅ" እየተባለ የሚጠቀስ) አፀደቀች።[63]**

**አዋጁ በኢትዮጵያ በ1952ቱ የፍትሐ ብሔር እና በ1957ቱ የፍትሐ ብሔር የሥነ-ሥርዓት ሕጎች ውስጥ ተካትተው ይገኙ የነበሩ ድንጋጌዎችን የማሰባሰብና የማሳደግ ሥራ ውጤት ነው።[64] ሕግ አውጪው ይህንን አዋጅ ሲያፀድቅ ከባዶ (በእንግሊዘኛው "ታቡላ ራሳ" ከሚባለው) አይደለም የተነሳው። ከታሪካዊ ጠቀሜታው አንፃር አዲሱ የቀደሙትን ድንጋጌዎች በንፅፅር ማንሳት ቢቻልም አዲሱን አዋጅ በራሱ ከመመዘን አንፃር ግን ንፅፅራዊ ትንተናው ብዙም ፋይዳ አይኖረውም።[65] ይህ ክፍል ትኩረት የሚያደርገው በአዲሱ አዋጅ ልዩ ግምት በሚሰጣቸው ድንጋጌዎች ላይ ነው።**

---

[61] በዚህ ጉዳይ ላይ ይህን ፅሁፍ ይመልከቱ፡- New York Arbitration Convention, Ethiopia Ratifies the New York Convention, NEWYORKCONVENTION.ORG, https://www.newyorkconvention.org/news/ethiopia+ratifies+the+new+york+convention [https://perma.cc/YFZ6-BGTY] (last visited Jul. 11, 2021).

[62] የኒውዮርክ ኮንቬንሽን የአባል ሃገራትን ዝርዝር እዚህ ድረ-ገፅ ይመልከቱ፡- https://www.newyorkconvention.org/countries [https:// perma.cc/4V2Y-88UJ]

[63] የግልግልና ዕርቅ የሥራ ሂደት አዋጅ ቁጥር 1237/2013 [ከዚህ በኋላ "የኢትዮጵያ የግልግል ዳኝነት አዋጅ" እየተባለ የሚጠቀስ]

[64] ምንም እንኳን አዋጁ በአብዛኛው ቀደም ሲል የነበሩ ድንጋጌዎችን መልሶ ያካተተ ቢሆንም፣ ብዙ ቀደም ሲል የነበሩ ድንጋጌዎችንም በግልፅ ሽሯል። *ዝኒ ከማሁ፥* አንቀጽ 78።

> **አንቀጽ 78፡-** ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች፡- 1/ ከአንቀጽ 3318 እስከ 3324 ስለ ዕርቅ የተደነገጉት የፍትሐ ብሔር ሕግ ድንጋጌዎች እና ከአንቀጽ 3325 እስከ 3346 ስለ ቤተ-ዘመድ ዳኛ የተደነገጉት ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል። 2/ የቤተ-ዘመድ ዳኛን የሚመለከቱት የፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ከአንቀጽ 315 እስከ 319፣ 350፣ 352፣ 355-357 እና 461 በዚህ አዋጅ ተሽረዋል። 3/ ይህን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ሌላ ህግ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።
>
> **አንቀጽ 79፡-** ተፈጻሚነት ያላቸው ሕጎች፡- የእርቅ ወይም የግልግል ዳኝነት ሒደቱን ወይም ከሂደቱ ጋር ግንኙነት ያላቸው ይህንን አዋጅ የማይቃረኑ የፍትሐ ብሔር ሥነ-ስርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

[65] አዋጁ ወደ ኋላ ተፈጻሚነት አይኖረውም። *ዝኒ ከማሁ፥* አንቀጽ 77። አንቀጽ 77 እንዲህ ይላል፡-

> **የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች፡-** 1/ ይህ አዋጅ በስራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተፈረሙ የግልግል ዳኝነት ስምምነቶች አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በነበሩ ሕጎች መሰረት የሚገዙ ይሆናል። 2/ ይህ አዋጅ

ምንም እንኳን አዋጁ ከፍትሐ ብሔር ሕጉና ከፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ጋር አይቀሬ በሆነ መልኩ ቁርኝነቱን ቢያሳይም፥ በቅርቡ የፀደቀውን የኒውዮርክ ኮንቬንሽን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልገውን ያህል የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሞዴል የንግድ ሕግ ድንጋጌዎችን[66] ጨምሮ ከተለያዩ ምንጮች ሐሳብ ወስዷል። [67]

አዋጁን ለማውጣት አስፈላጊ ከሆኑባቸው ምክንያቶች አንደኛው "ከግልግል ዳኝነትና ከዕርቅ ጋር በተያያዘ የዳበሩ ዓለም አቀፍ አሠራሮችንና መርሆዎችን ታሳቢ በማድረግ በሥራ ላይ ያሉ ሕጎችን ማሻሻል አስፈላጊ በመሆኑ" ነው። [68]

### *3.2.1. የተፈፃሚነት ወሰን*

አዋጁ በብሔራዊና ዓለም አቀፍ የግልግል ዳኝነቶች ላይ ተፈፃሚ ነው። አዋጁ ዓለም አቀፍ የግልግል ዳኝነትን የሚተረጉመው የተዋዋይ ወገኖችን ዋነኛ የቢዝነስ ቦታ እና/ወይም የውል ግንኙነቱ የሚፈፀምበትን ቦታ በማጣመር ነው። [69]

---

*ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተጀመሩ የግልግል ዳኝነቶች ወይም የግልግል ዳኝነትን በተመለከተ በፍርድ ቤቶች በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮች፣ የክርክር ሂደቶችና እና የተሰጡ ውሳኔዎች አፈጻጸም ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በነበሩ ህጎች መሰረት ይታያሉ። 3/ ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የግልግል ዳኝነት ስምምነት የፈፀሙ ወይም በሂደት ላይ ያሉ ተዋዋይ ወገኖች በዚህ አዋጅ መሰረት ለመዳኘት መስማማት ይችላሉ።*

[66] United Nations Commission on International Trade Law, UNCITRAL Model Law on International Commercial Arbitration *(1985)* [**ከዚህ በኋላ** "UNCITRAL Model Law" **እየተባለ የሚጠቀስ**], UNCITRAL.UN.ORG. https://uncitral.un.org/en/texts/arbitration/modellaw/commercial_arbitration [https://perma.cc /4V2Y-88UJ]

[67] የኢትዮጵያ የግልግል አዋጅ፣ *በግርጌ ማስታወሻ ቁ.* 63 የተቀመጠ፣ *መቅድም፡- "ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸው እና ያጸደቀቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ተግባራዊ ለማድረግ ይረዳል"።*

[67] *ዝኒ ከማሁ።*

[68] *ዝኒ ከማሁ።*

[69] የኢትዮጵያ የግልግል አዋጅ፥ *በግርጌ ማስታወሻ ቁ.* 63 የተጠቀሰ፥ አንቀጽ 4።

*1/ አንድ የግልግል ዳኝነት ከዚህ በታች ከተመለከቱት በአንዱ ሥር የሚወድቅ ከሆነ ዓለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት እንደሆነ ይቆጠራል፡- ሀ) ተዋዋይ ወገኖች የግልግል ስምምነት በሚፈጽሙበት ወቅት ዋነኛ የቢዝነስ ቦታቸው በሁለት የተለያየ ሀገራት የነበረ ሲሆን፣ ለ) በግልግል ዳኝነት ስምምነቱ የተመረጠ የግልግል ዳኝነቱ ህጋዊ መቀመጫ ወይም በንግድ ወይም በውል ግንኙነት ውስጥ ያሉ ዋነኛ ግዴታዎች የሚፈፀምባቸው ወይም አለመግባባቱ የተከሰተበትና የተያያዘበት የተዋዋይ ወገኖች ዋነኛ የቢዝነስ ቦታ ውጭ ሀገር ሲገኝ፣ ሐ) ተዋዋይ ወገኖች የግልግል ዳኝነት ስምምነቱ ጉዳይ ከአንድ በላይ ከሆኑ ሀገሮች ጋር የተያያዘ መሆኑን በግልጽ ሲስማሙ። 2/ ለዚህ አንቀጽ ተፈጻሚነት ሲባል ተዋዋይ ወገኖች ከአንድ በላይ የቢዝነስ ቦታ ያላቸው ሆኖ ሲገኝ*

### 3.2.2. የግልግል ዳኝነት ስምምነት ፎርም፣ የግልግል ዳኝነት ስምምነትን ስለማስፈፀምና ጉባዔው ሥልጣኑን በራሱ መወሰን ስለመቻሉ

የግልግል ዳኝነት ስምምነት ተቀባይነትን እንዲያገኝ የኒውዮርክ ኮንቬንሽን በፅሁፍ መደረግ እንዳለበት ከሚደነግገው ጋር ተመሳሳይነት ባለው መልኩ፣ የግልግል ዳኝነት አዋጁ ይህንኑ በጥቂቱ በማሻሻልና የዘመኑን የመረጃ መያዣ ሥርዓት በመቀበል ለኤሌክትሮኒክ መገናኛ ዘዴም እውቅናን ሰጥቷል።[70] በማያሻማ መልኩ "የኤሌክትሮኒክ ግንኙነት"ን እንዲህ በማለት ተርጉሞታል፥ "... ማንኛውም በኢሜይል የሚደረግ የመረጃ ልውውጥ ወይም በኤሌክትሮኒክ፣ በማግኔቲክ፣ በኦፕቲካል ወይም ተመሳሳይ በሆኑ ዘዴዎች ተዋዋይ ወገኖች የሚያደርጉት የመረጃ መላክ፣ መቀበል ወይም ማከማቸት ተግባር ነው።"[71]

የግልግል ዳኝነት ስምምነቱ "የማይፀና ወይም ተፈፃሚ" ስለመሆኑ ጉዳዩ የሚመለከተው ፍ/ቤቱ ካልወሰነ በስተቀር የግልግል ዳኝነት ስምምነቶች ተፈፃሚ ናቸው።[72] ምንም እንኳን ግቡ የግልግል ዳኝነት ስምምነትን ተፈፃሚ የሚያደርገውን የኒውዮርክ ኮንቬንሽንን አንቀጽ II ተፈፃሚ ማድረግ ቢሆንም፣ የግልግል ዳኝነቱን ስምምነት ተፈፃሚ ለማድረግ ወይም ውሳኔን ስለሚሰጠው አካል ስልጣን የተለየ መመዘኛን (ስታንዳርድ) ስለማስቀመጡ ግልፅ ባይሆንም፣ አዋጁ በአንቀጹ አቀራረፅ ላይ ለውጥ አድርጓል። ለውጦቹን በሚከተለው የአንቀጽ አቀራረፆች ውስጥ እንመለከታለን።

> በአንድ የግልግል ዳኝነት ስምምነት ውስጥ በሚወድቅ አለመግባባት ላይ ለፍርድ ቤት ክስ ሲቀርብና ተከሳሹ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የግልግል ዳኝነት ስምምነት ያላቸው በመሆኑ በዚያው አግባብ መታየት እንዳለበት ተቃውሞውን ካቀረበ ፍ/ቤት ክሱን ውድቅ በማድረግ በግልግል ዳኝነት ስምምነቱ መሠረት ጉዳያቸውን እንዲጨርሱ ሊያሰናብታቸው ይገባል።[73]

ይሁን እንጂ ይህ ዓይነቱ ድንጋጌ ቢኖርም ፍ/ቤቱ "...የግልግል ዳኝነት ስምምነቱ የማይሆን በሆነ ጊዜ ጉዳዩን ለማየት ይችላል።"[74] የኒውዮርክ ኮንቬንሽን ደግሞ እንዲህ በማለት ደንግጓል፡-

---

ለግልግል ስምምነቱ ቅርበት ያለው የቢዝነስ ቦታ እና ምንም የቢዝነስ ቦታ የሌላቸው ከሆነ የተዋዋይ ወገኖች መደበኛ መኖሪያ ቦታ እንደ ዋነኛ የቢዝነስ ቦታቸው ተደርጎ ይወሰዳል።

[70] ዝኒ ከማሁ፥ አንቀጽ 6(1-4)።

[71] ዝኒ ከማሁ፥ አንቀጽ 6(5)።

[72] ዝኒ ከማሁ፥ አንቀጽ 8(2)።

[73] ዝኒ ከማሁ፥ አንቀጽ 8(1)።

[74] ዝኒ ከማሁ፥ አንቀጽ 8(1)።

> በዚህ አንቀጽ መሠረት በግልግል ዳኝነት የሚፈታ ጉዳይ ወደ ፍርድ ቤት ቀርቦ እንዲታይ ጥያቄ ከቀረበበት ፍርድ ቤቱ የግልግል ዳኝነት ስምምነቱ ዋጋ ያጣና ፈራሽ፤ የማይተገበር ወይም ሊፈፀም የማይችል መሆኑን ካላረጋገጠ በቀር ከተከራካሪ ወገኖች ባንደኛው ጥያቄ መሰረት ጉዳዩ በግልግል ዳኝነት እንዲፈታ ይመራዋል።[75]

በኮንቬንሽኑ የተደረደሩት "ዋጋ ያጣና ፈራሽ (null and void)፣ የማይተገበር (inoperative) ወይም ሊፈፀም የማይችል (incapable of being performed)" የሚሉት የእያንዳንዱ ቃላት ትርጉም ለሰፊ ሙግት የበቁ ናቸው።[76] ባሁኑ ሰዓት ግን በእያንዳንዱ ቃል ላይ መግባባት የተደረሰበት የሕግ ሳይንስ ተፈጥሯል። የኢትዮጵያ ሕግ አውጪ የቃላት ለውጦችን ለምን እንዳደረገ በግልፅ ባይታወቅም፤ "የሚሻርና የማይፀና፣ የማይተገበር ወይም ሊፈፀም የማይችል" ከሚሉት ቃላት ጋር ተመሳሳይ ትርጉም የያዙ ሌላ ቃላትን ተጠቅሟል።

የፀና የግልግል ዳኝነት ስምምነት ስለመኖሩ መወሰን ያለበት ፍርድ ቤት ነው ወይስ የግልግል ዳኝነት ጉባዔው ለሚለው ጉዳይ አዋጁ የኒውዮርክ ኮንቬንሽንን ተፈፃሚ በማድረግ ረገድ በስፋት ተቀባይነትን ካገኘው ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአለም አቀፍ ንግድ ሕግ ሞዴል ድንጋጌ እጅጉን ርቋል። የሞዴል ሕጉ አንቀጽ 16 እንዲህ በማለት ይደነግጋል፡-

> ጉባዔው ስልጣኑን በራሱ መወሰን ስለመቻሉ፡- (1) የግልግል ዳኝነት ስምምነት መኖርና አለመኖርን አስመልክቶ የሚቀርብ ተቃውሞን ጨምሮ ጉባዔው ሥልጣኑን ለመወሰን ሊወስን ይችላል። ለዚህ ሲባል በስምምነት ውስጥ የተቀረፀው የግልግል ዳኝነት አንቀጽ ከሌሎቹ የስምምነቶቹ አንቀፆች ተነጥሎ በራሱ እንደቆመ ስምምነት ይቆጠራል። ጉባዔው ስምምነቱ (ውሉ) ዋጋ ያጣና ፈራሽ (null and void) ነው በማለት መወሰኑ የግልግል ዳኝነት አንቀጹን በሕግ አግባብ *(ipso jure)* ዋጋ ሊያሳጣው አይችልም።[77]

ይህ አንቀጽ ጉባዔው ሥልጣኑን በራሱ መወሰን ይችላል የሚለውን (competence-competence) መርህና ከዋናው ውል የተለየና ራሱን የቻለ (separability) በመባል

---

[75] Convention on the Recognition and Enforcement of Foreign Arbitral Awards, art. II (3), June 10, 1958, 21 U.S.T. 2517, 330 U.N.T.S. 3 [ከዚህ በኋላ "New York Convention" እየተባለ የሚጠቀስ].

[76] በእነዚህ ርዕሶች ላይ የተደረጉ ውሳኔዎችን ከሚከተለው ምንጭ ማግኘት ይቻላል፡- New York Arbitration Convention Court Decisions. New York Arbitration Convention, Court Decisions, newyorkconvention.org, https://www.newyorkconvention.org/court+decisions [https://perma.cc/A9QB-42UW].

[77] UNCITRAL Model Law, *በግርጌ ማስታወሻ ቁ.* 66 የተጠቀሰ፥ አንቀጽ16(1)።

የሚታወቁትን ሁለት መርሆዎችን ያቀፈ ነው። እነዚህ ሁለት የታወቁ መርሆዎች የብሔራዊም ሆነ የዓለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት የሕግ ሥርዓቶች ዋነኛ ምሰሶዎች ናቸው።

በጥቂቱም ቢሆን ለየት ባለ ቋንቋ ቢቀረፅም የኢትዮጵያው አዋጅም ጉባዔው ሥልጣኑን በራሱ መወሰን ይችላል የሚለውን መርህና ከዋናው ውል የተለየና ራሱን የቻለ ነው የሚለውን ሌላኛውን መርህ አካትቶ የያዘ ነው።

> በተዋዋይ ወገኖች መካከል የፀና የግልግል ዳኝነት ስምምነት መኖር አለመኖርን ጨምሮ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን አለኝ ወይም የለኝም በሚለው ላይ ጉባዔው የመወሰን ሥልጣን አለው። ለዚህ ዓላማ ሲባል በአንድ ዋና ውል ውስጥ የተካተተ የግልግል ዳኝነት አንቀጽ ከዋናው ውል እንደተለየ እና ራሱን እንደቻለ ውል ይቆጠራል፤ የዋናው ውል ፈራሽ እና ዋጋ የሌለው መሆን የግልግል ዳኝነት አንቀጹን ዋጋ እንዲያጣ እና ፈራሽ እንዲሆን አያደርገውም።[78]

ነገር ግን የግልግል ዳኝነት ጉባዔው ከፍ/ቤቱ የተለየ ውሣኔን በማሳለፍ ጉዳዩን የተወሳሰበ ሊያደርገው እንደሚችል ከወዲሁ ማመን ይቻላል።[79] ከዚህ አንፃር እነዚህን ሁለት

---

[78] የኢትዮጵያ የግልግል አዋጅ፥ *በግርጌ ማስታወሻ ቁ.* 63 የተጠቀሰ፥ አንቀጽ 19(1)።

[79] ይህ ሁኔታ በሚከተለው ታዋቂ የአሜሪካ ሀገር ፍርድ የታየ ጉዳይ ነው፡- Kulukundis Shipping Co. v. Amtorg Trading Corp., 126 F.2d 978, 986 (2d Cir. 1942).

> (b) If the issue of the existence of the charter party were left to the arbitrators and they found that it was never made, they would, unavoidably (unless they were insane), be obliged to conclude that the arbitration agreement had never been made. Such a conclusion would (1) negate the court's prior contrary decision on a subject which, admittedly, the Proclamation commits to the court, and (2) would destroy the arbitrators' authority to decide anything and thus make their decision a nullity.

> [(ለ) የቻርተር ፓርቲው የመኖር ጉዳይ ለግልግል ዳኞች ከተተወ እና ፈፅሞ እንዳልተደረገ ከደመደሙ፥ ያለማወላወል (እብዶች ካልሆኑ በቀር) የግልግል ስምምነቱ ፈጽሞ አልተደረገም ብለው ለመደምደም ይገደዳሉ። እንዲህ ዓይነቱ መደምደሚያ፡- (1) ፍርድ ቤቱ ቀደም ሲል በተመሳሳይ ጉዳይ በአዋጁ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የሰጠውን ውሳኔ የሚቃረን ይሆናል፤ እንዲሁም፥ (2) የግልግል ዳኞች በማናቸውም ጉዳይ የመወሰን ሥልጣናቸውን የሚያጠፋና ውሳኔያቸውንም ውድቅ ያደርገዋል።]

> Philip G. Phillips, The Paradox in Arbitration Law*:* Compulsion as Applied to a Voluntary Proceeding, 46 HARV. L. REV. 1258, 1270-1272 (1933); Philip G. Phillips, A *Lawyer's* Approach to Commercial Arbitration, 41 YALE L.J. 31 (1934); GEORGE J. WILLISTON, WILLISTON ON CONTRACTS 5369-5379 (Rev.ed.1938). Although this case's significance is on separability and is now outdated, it's description of the competence-competence anomaly is still instructive.

መርሆዎች አስመልክቶ የኢትዮጵያው አዋጅ የተከተለው አቀራረጽ በግልግል ዳኝነት የሕግ ሳይንስ ውስጥ ሁሌ ችግር ሆነው ለሚነሱ ለነዚህ ጉዳዮች መፍትሄን አልሰጠም። [80]

### 3.2.3. ለግልግል ዳኝነት ስለሚቀርቡና ስለማይቀርቡ ጉዳዮች

የሕዝብ ጠቀሜታን የተመለከቱ የሕግ ጉዳዮችን አስመልክቶ የአሜሪካ ጠቅላይ ፍ/ቤት እ.አ.አ. በ1984 በ"ሚትስቡሽና በሶለር" ላይ ውሳኔን ካሳለፈ ጊዜ ጀምሮ ከዚህ ቀደም በዓለማችን ለግልግል ዳኝነት መዝገብ[81] የማይቀርቡ ተብለው ተገድበው የነበሩ ጉዳዮች በየጊዜው እየተቀናነሱ በመሄድ ላይ ናቸው።

በ"ሚትስቡሺና በሶላር" የክርክር ጉዳይ ላይ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ "የሸርማን ሕግ"[82] በመባል የሚታወቀውን የአሜሪካንን የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃን አዋጅ መሰረት በማድረግ የሚነሱ የክስ ምክንያቶች በግልግል ዳኝነት ሊታይ እንደሚችል በመፍቀዱ ዓለም አቀፍ የግልግል ዳኝነትን[83] በሚያበረታታ መልኩ በ"ብሬመን እና ዛፐታ" መካከል በነበረው ክርክር የተጀመረው ሂደት ተጠናክሮ እንዲቀጥል አድርጓል። [84]

የኢትዮጵያው የግልግል ዳኝነት አዋጅም በግልግል ዳኝነት የማይታዩ ዝርዝር ጉዳዮችን ለይቶ አስቀምጧል። የሚከተሉት ጉዳዮች ለግልግል ዳኝነት አይቀርቡም፡-

1. የፍች፣ የጉዲፈቻ፣ የአሳዳሪነት፣ የሞግዚትነትና የውርስ ጉዳዮች፤
2. የወንጀል ጉዳዮች፤
3. የግብር ጉዳዮች፤
4. መክሰር ላይ የሚሰጥ ውሳኔ፤
5. የንግድ ማህበራት ላይ የሚሰጥ ውሳኔ፤

---

[80] መሰረታዊው የግልግል ዳኝነት ሥነ-ሕግ ከግልግል ስምምነቶች አፈፃፀም ጋር በተያያዘ የፍርድ ቤቶች እና የግልግል ተቋማት ሚና(ስልጣን) ምን መሆን እንዳለበት ለመለየት ይመረምራል። በዚህ ጉዳይ ላይ በጣም አስተማሪ ሁለት ፍርዶች የሚከተሉት ናቸው፡- Fiona Trust Holding Corp and Ors v. Privalov and Ors [2006] EWHC 2583 (Comm); Buckeye Check Cashing, Inc. v. Cardegna, 546 U.S. 440 (2006); First Options of Chicago, Inc. v. Kaplan, 514 U.S. 938 (1995).

[81] Mitsubishi v. Soler Chrysler-Plymouth, 473 U.S. 614 (1985).

[82] *ዝኒ ከማሁ፥ ከገፅ* 473-73።

[83] ይህ በመሰረቱ በ Wilko v. Swan ፍርድ አንፃኦት የተሰጠውንና በብዙ ቀደምት ፍርዶች የተመለከተውን 'የኢንቨስተሮችን ደህንነት የሚመለከቱ ጉዳዮች ለግልግል ዳኝነት አይቀረቡም' የሚለውን ደንብ ይሽራል። Wilko v. Swan, 346 U.S. 427, 438 (1953).

[84] The Bremen v. Zapata Off-shore Co., 407 US 1, 9-10 (1972).

6. የሊዝ ጉዳይን ጨምሮ አጠቃላይ የመሬት ጉዳዮች፤
7. አስተዳደራዊ ውሎች፥ በልዩ ሁኔታ ካልተፈቀደ በቀር፤
8. የንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ፤
9. በሕግ ለሚመለከታቸው አስተዳደራዊ አካላት በተሰጠ ሥልጣን ስር የሚሸፈኑ አስተዳደራዊ አለመግባባቶች፤
10. በግልግል እንዳይታዩ በሕግ የተከለከሉ ሌሎች ጉዳዮች። [85]

ይህ ዝርዝር እ.አ.አ. በ1980ዎቹ ወይም ከዛ በፊት በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች ተዘርዝረው ከነበሩት ጋር ተመሳሳይነት አለው። እየዘመነ የመጣውን የድንበር ተሻጋሪ ንግድ ጉዳይ ፍላጎት ከግምት በማስገባት ቀድሞ በ“ዊልኮ እና ስዋን”[86] መዝገብ ላይ የተወሰነውን በመሻር በ“ሚትስቡሽና በሶለር” እንዲሁም በ“ሮድሪገዝ ዴ. አውጃስ እና ሼርሰን /አሜሪካን ኤክስፕሬስ ኢንክ” መዝገቦች ላይ ጉዳዩ በግልግል ዳኝነት ሊታይ እንደሚችል በመወሰኑና ዓለም አቀፋዊ ተቀባይነትን ካገኘው አካሄድ ጋር መጣጣሙ፤ በተቃራኒው ደግሞ ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው በኢትዮጵያው አዋጅ አንቀጽ 7(8) ላይ “የንግድ ውድድርና ሸማቾች” ጉዳይ በግልግል ዳኝነት ከማይታዩ ጉዳዮች ተርታ መግባቱ ትኩረትን የሚስብ ጉዳይ አድርጎታል። በ1980ዎቹ በብዙ ሀገሮች የነበሩ ዘመናዊ ዕድገትን[87] የሚፃረሩ መርሆዎችን

---

[85] የኢትዮጵያ የግልግል ዳኝነት አዋጅ፥ *በግርጌ ማስታወሻ ቁ.* 63 የተጠቀሰ፥ አንቀጽ 7።

[86] Wilko v. Sawn was overruled by Rodriguez de Quijas v. Shearson/American Express Inc., 490 U.S. 477, 486 (1989). (“Our conclusion is reinforced by our assessment that resort to the arbitration process does not inherently undermine any of the substantive rights afforded to petitioners under the Securities Act.”)

[87] በአውሮፓ ግዛቶች ውስጥ ስላለው ስለእነዚህ ዘመናዊ አዝማሚያዎች ማብራሪያ ይህን ሰነድ ይመልከቱ፡- Komninos, Assimakis, Arbitration and EU Competition Law, (April 12, 2009). Available at SSRN: https://ssrn.com/abstract=1520105. “All these elements of competition law had led in the past to the exclusion of the arbitrability of antitrust-related disputes, because of their public policy (ordre public) nature. This attitude, however, was reversed in the 1980s and early 1990s and it can now be said with certainty that arbitrability of competition law disputes is generally accepted in all jurisdictions with developed antitrust regimes.” (“ቀደም ሲል እነዚህ ሁሉ የውድድር ህግ ደንቦች የፐብሊክ ፖሊሲ ፀባይ ያላቸው በመሆኑ ከፀረ-ውድድር (anti-trust) ጋር የተገናኙ ጉዳዮች በግልግል ዳኝነት እንዳይታዩ ይከለከል ነበር። ይሁን እንጂ ይህ አመለካከት በ1980ዎቹ እና በ1990ዎቹ መጀመሪያ ላይ ተቀልብሶ በአሁኑ ጊዜ ከውድድር ሕግ ጋር የተያያዙ አለመግባባቶችን በግልግል መፍታት በአጠቃላይ በሁሉም የዳበረ ፀረ-ውድድር (anti-trust) የህግ ስርአት ባለባቸው ሀገሮች ሁሉ ተቀባይነት እንዳለው በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል።”) Citing numerous useful authorities beyond the US cases cited above. Some more useful authorities cited include: in France CA Paris, 19.5.1993, Labinal SA v. Mors and Westland Aerospace Ltd., (1993) Rev.Arb. 645; In Italy, Corte di Cassazione, 21.8.1996, no. 7733, Telecolor SpA v. Technocolor SpA, 47 Giust.Civ. I-1373 (1997); In England &Wales, ET Plus SA et al. v. Welter et al. (Comm.), [2006] Lloyd’s Rep. 251; [2005] EWHC 2115.

በመሻር በአዲስ የተካውን አካሄድ በሚፃረር መልኩ የኢትዮጵያው የ2013ቱ አዋጅ ቀሪ የተደረጉ መርሆዎችን አካቶ ይዟል።

በተመሳሳይ መልኩ ሌሎች ትኩረት ከሚሹ ለግልግል ዳኝነት የማይቀርቡ ተብለው ከተያዙ ዝርዝሮች መካከል በንዑስ አንቀጽ 7 ሥር የተመለከተውን "በልዩ ሁኔታ ካልተፈቀደ በስተቀር" የአስተዳደራዊ ውሎች፣ እንዲሁም በንዑስ አንቀጽ 9 ሥር የተመለከተውን "በሕግ ለሚመለከታቸው አስተዳደራዊ አካላት በተሠጠ ሥልጣን ሥር የሚሸፈኑ አስተዳደራዊ አለመግባባቶች" የሚሉት ይገኙበታል።

ወደፊት የሚወጡ ሌሎች ሕጎች ወይም ፍ/ቤቶች የሚሰጧቸው የሕግ ትርጉሞች የእነዚህን ገደቦች ምንያህሌነት የሚወስኑት ቢሆንም፣ አስተዳደራዊ ውሎች በግልግል ዳኝነት መታየት ስላለባቸው ጉዳይ በቀደምት ሕግጋቱም ቢሆን ብዥታ የነበረበት ነበር።[88] አስተዳደራዊ ውሎች በግልግል ዳኝነት የማይታዩ ጉዳዮች ሆነው የተቀረፁት በኢትዮጵያ ብቻ አይደለም። መሠረቱና ምንጩም ብዙዎቹ የሲቪል ሕግ ሥርዓት ተከታዮች የተቀበሉት (እ.አ.አ.) የ19ኛው ክፍለ ዘመን የፈረንሳይ ሕግ ነው። ይሁን እንጂ አሁን ያለው የዘመነው ዝንባሌ ግን አስተዳደራዊ ውሎችም ቢሆኑ በግልግል ዳኝነት እንዲታዩ መፍቀድ ነው። ሚ/ር ጌሪ ቦርን ይህን አስመልክቶ በጥቅሉ እንዲህ በማለት ፅፏል:-

> ያለፉት አራት አሥርት አመታት የፈረንሳይ የሕግ እድገት ውጤት ዓለም አቀፍ ይዘት ያላቸው አስተዳደራዊ ውሎች በግልግል ዳኝነት አይታዩም የሚለውን ገደብ በአብዛኛው የቀነሰ ነው። የፍትሐ ብሔር ሕጉ ለግልግል ዳኝነት በማይቀርቡ ጉዳዮች ላይ በስፋት (እና ኋላቀር) በሆነ መልኩ የደነገገው ቢኖርም፥ እንዲሁም እነዚህ ድንጋጌዎች በተመሳሳዩ በስፋት ታሪካዊ ትርጉም የተሰጠባቸው ቢሆኑም፥ የፈረንሳይ ፍ/ቤቶች ለግልግል ዳኝነት የማይቀርቡ ጉዳዮችን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያጠበቧቸው መጥተዋል። በውጤቱም ለግልግል ዳኝነት የማይቀርቡ ጉዳዮች ተብለው የሚታዩት አስገዳጅ በሆነ ወጥ ሕግ (ድንጋጌ) ውስጥ በግልፅ ተለይተው የተቀመጡ ጉዳዮች ብቻ ናቸው። በቅርቡም በተከለሰው የፈረንሳይ የግልግል ዳኝነት ሕግ ውስጥ ይህን የሚለውጥ ውጤት አልተመለከተም።[89]

[88] በቀድሞው የኢትዮጵያ የግልግል ሕግ ላይ የበለጠ ማብራሪያ ለማግኘት ይህን ፅሁፍ ይምልከቱ:- Zekarias Keneaa, Arbitrability in Ethiopia: Posing the Problem, J. OF ETHI. LAW VOL. XVII (1994).

[89] GARY B. BORN, INTERNATIONAL COMMERCIAL ARBITRATION 964 (2nd ed.), at 957-1045.

**የተለየ ባይሆንም[90] የኢትዮጵያ የግልግል ዳኝነት አዋጅ የተቃራኒውን ጎራ በመያዝ ይህ ጉዳይ በግልግል ዳኝነት ሊታይ የሚችለው በግልፅ በሕግ ሲፈቀድ ብቻ ነው ይላል። በመሆኑም ድንበር ተሻጋሪ በሆኑ የአስተዳደር ውሎች ውስጥ የገቡ የግልግል ዳኝነት አንቀፆች ተፈፃሚ የሚሆኑት የግልግል ዳኝነት አዋጅ በጥቅሉ የከለከለውን ልዩ ሕጉ በግልፅ ከፈቀደ ብቻ ነው።**

**ሰፋት ባለው መልኩ ይህን ገደብ የሚጥሰው የኢንቨስትመንት አዋጅ እንዲህ በማለት ይደነግጋል። "2/ የፌደራል መንግስት የውጭ ኢንቨስትመንትን በተመለከተ የሚነሱ የኢንቨስትመንት አለመግባባቶች በግልግል ዳኝነት እንዲፈቱ ሊስማማ ይችላል።"[91] ይህ አንቀጽ አስተዳደራዊ ውሎች "በሕግ ካልተፈቀደ በስተቀር" ለግልግል ዳኝነት የማይቀርቡ ጉዳዮች መሆናቸውን ከሚደነግገው የግልግል ዳኝነት አንቀጽ 7(7) ጋር ተጣምሮ ሲነበብ በግልፅ የሚያሳየው የግልግል ዳኝነቱ አዋጅ በስራ ላይ ከዋለ በኋላ በፌደራል መንግስት ተቋማት የተፈረሙ ኢንቨስትመንትን የተመለከቱ አስተዳደራዊ ውሎች በግልግል ዳኝነት ሊታዩ እንደሚችሉ ነው።**

**ሌሎች በልዩነት ሊጠቀሱ የሚገባቸው ምሳሌዎች ዘርፍ ተኮር ናቸው። የማዕድን *ሥራ* አዋጅ ቁጥር 678/2010[92] እንመልከት። አግባብነት ያለው አንቀጽ እንዲህ ይላል፡- "ጉዳዩ በጋራ ውይይት ሊፈታ ካልቻለ በስምምነት ውስጥ በተመለከተው *ሥነ-ሥርዓት* መሠረት በግልግል ዳኝነት ታይቶ ይወሰናል። በግልግል ዳኝነት የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻና በተዋዋይ ወገኖች ላይ የፀና ይሆናል።"[93]**

---

[90] **ለንፅፅር የግብፅን ሕግ ይመልከቱ፡-** Law No. 27/1994 Promulgating the Law Concerning Arbitration in Civil and Commercial Matters [hereinafter Egyptian Arbitration Law] available at http://www.crcica.org.eg/LawNo271994.pdf [https://perma.cc/3ETQ-64XG]. **ውሉ በሚደረግበት ጊዜ የሚመለከተው ሚኒስትር ካልፈቀደ በቀር ከአስተዳደራዊ ውሎች ጋር የተያያዙ አለመግባባቶች ለግልግል እንደማይቀርቡ ይደነግጋል። በዚህ ነጥብ ላይ አጠር ላለ ማብራሪያ የሚከተለውን ፅሁፍ ይመልከቱ፡-** Fatma Salah, New Approval Required for Government Contracts and Arbitration Agreements in Egypt, Kluwer Arbitration Blog, Feb. 21, 2021, http://arbitrationblog.kluwerarbitration.com/2021/02/21/new-approval-required-for-government-contracts-and-arbitration-agreements-in-egypt/ [https://perma.cc/7UD4-FUHV].

[91] **የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር** 1180/2012፥ ***በግርጌ ማስታወሻ ቁ.*** 30 **የተጠቀሰ፥ አንቀፅ** 28(2)።

[92] **ማዕድን የማውጣት አዋጅ ቁጥር** 678/2010።

[93] ***ዝኒ ከማሁ፥*** **አንቀጽ** 76(2)። **የቀሩት የዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ክፍሎች፡-**

> 76. **አለመግባባቶችን ስለመፍታት፡-** 1/ **የማዕድን ቅኝት፣ ምርመራ፣ ይዞ መቆየት ወይም ማምረትን ከተመለከተ ስምምነት በመነጨ፣ በስምምነቱ አተረጓጎም፣ መጣስ ወይም መቋረጥ ምክንያት ወይም ከእነዚሁ ጋር በተያያዙ ምክንያቶች በመንግስትና በባለፈቃድ መካከል የሚፈጠር**

የነዳጅ ሥራዎች አዋጅ ቁጥር 295/1978 በተመሳሳዩ እንዲህ በማለት ይደነግጋል፡- "፪/ ጉዳዩ በጋራ ውይይት ሊፈታ ካልቻለ በነዳጅ ስምምነት ውስጥ በተመለከተው ሥነ-ሥርዓት መሠረት በግልግል ዳኝነት ታይቶ ይወሰናል።"[94]

ኢንቨስትመንትን የተመለከቱ የአስተዳደር ውሎችንና ዋና የተባሉ የተፈጥሮ ሀብት ዘርፎችን አስመልክቶ የአስተዳደር ውሎች ለግልግል ዳኝነት የማይቀርቡ መሆናቸውን የሚደነግገው አዲሱ የግልግል ዳኝነት አዋጅ ድንበር ተሻጋሪ ለሆኑ ከፍተኛ ጉዳዮች ብቻ በልዩ ሁኔታ የሚፈቀድበትን አግባብ አመቻችቷል።

### *3.2.4. የግልግል ዳኞችና የግልግል ዳኝነት ተቋማት*

አዋጁ ተዋዋይ ወገኖች በዜግነት ላይ ልዩነት ሳያደርጉ የግልግል ዳኞቻቸውን መምረጥ እንደሚችሉና፣ አንደኛው ወገን ዳኛን ለመምረጥ ካልፈለገ ወይም በጋራ ሦስተኛ ዳኛን መምረጥ ካልቻሉ ዳኛን የመሰየም ሥልጣኑን ለፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሠጥቷል።[95] ፍርድ ቤቱ በግልግል ዳኞች አሿሿም ላይ የሚሰጠው ውሳኔ ይግባኝ የማይቀርብበት ነው።[96] የአንድን የግለግል ዳኛ ገለልተኛነትና ነፃነት መሠረት አድርጎ የሚነሳ ተቃውሞ በመጀመሪያ በራሱ በግልግል ዳኝነት ጉባዔው ውድቅ የተደረገበት ሰው ቅሬታውን ይግባኝ ለማይቀርብበት ውሳኔ ለፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሊያቀርብ ይችላል።[97] ቅሬታውን የመመዘኛው መስፈርትም በስፋት ተቀባይነትን ያገኘው "ገለልተኛነቱንና ነፃነቱን

> ማንኛውም ክርክር፣ አለመግባባት ወይም የይገባኛል ጥያቄ በተቻለ መጠን በጋራ ውይይት ይፈታል። … 3/ በግልግል ዳኝነት በሚሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ወገን ቅሬታውን ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ይግባኝ እንዲታይለት ማቅረብ ይችላል።

[94] አዋጅ ቁጥር 295/1986፥ የፔትሮሊየም ኦፕሬሽንን ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ፥ አንቀጽ 25(2)።

[95] የኢትዮጵያ የግልግል አዋጅ፥ *በግርጌ ማስታወሻ ቁ.* 63 የተጠቀሰ፥ አንቀፅ12(3)።

> (ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) የተደነገገው ቢኖርም አንደኛው ወገን ዳኛ እንዲመርጥ በሌላኛው ወገን ማስታወቂያ በተሰጠው በ30 ቀናት ውስጥ ዳኛ መምረጥ ካልቻለ ወይም ሁለቱም ዳኞች ከተመረጡ በ30 ቀናት ውስጥ የሦስተኛ ዳኛ ምርጫ ላይ መስማማት ካልቻሉ ወይም አንድ ዳኛ ባለበት የግልግል ዳኝነት ሁለቱም ወገኖች መስማማት ያልቻሉ እንደሆነ በአንደኛው ወገን ጠያቂነት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኛውን ይሰይማል።

[96] *ዝኒ ከማሁ፥* አንቀጽ 12(7)።

[97] *ዝኒ ከማሁ፥* አንቀጽ 15(4)። "ያቀረበው ተቃውሞ ውድቅ የተደረገበት ሰው ውጤቱ በተነገረው በ30 ቀናት ውስጥ ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቅሬታውን ማመልከት ይችላል፤ ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው ውሳኔ ይግባኝ አይቀርብበተም።"

ያጓደሉ አሳማኝ ጥርጣሬ ውስጥ የሚከቱ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ" በግልግል ዳኛው መመረጥ ላይ ቅሬታ ሊቀርብበት ይችላል የሚለው መርህ ነው። [98]

በአዋጁ ከተካተቱ አበይት ተጨማሪ ጉዳዮች አንደኛው በሀገር ውስጥ ሊቋቋሙ ስለሚችሉ የግልግል ዳኝነት ማዕከላት ማንሳቱ ነው። በመንግስት ወይም በግል ተቋቁመው ጎን ለጎን ሊሰሩ የሚችሉ ተቋማት እንደሚኖሩ ታሳቢ ያደርጋል። ከዚህ ጋር በተያያዘም አግባብነት ያለው የአዋጁ አንቀጽ የሚከተለውን ደንግጓል፡-

> II. የግልግል ዳኝነት ማዕከላት ፩/ የግልግል ዳኝነት በመንግስት ወይም በግል ሊቋቋም ይችላል። ፪/ የፌደራል ጠቅላይ አቃቤ ህግ የግልግል ዳኝነት ማዕከላትን ይቆጣጠራል፤ ፈቃድ ይሰጣል፤ ያድሳል፤ የሚቋቋሙበትን መስፈርቶች ያወጣል፤ ዝርዝሩ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል። ፫/ ይህ አዋጅ በስራ ላይ ያሉ የግልግል ዳኝነት ተቋማት እንዳይቀጥሉ አይከለክልም። [99]

ይህ ፅሁፍ እስከ ተዘጋጀበት ጊዜ ድረስ ዝርዝር ደንቡ ባይወጣም የጣልቃ ገብነት ደረጃው ወደተፈለገው አቅጣጫ ሊጎተት የሚችልን የመንግስትን የፍቃድ መስጠትና የመቆጣጠር ሥልጣንን ያካተተ ነው።

### 3.2.5. ጊዜያዊ የመጠባበቂያ እርምጃ

ጊዜያዊ የመጠባበቂያ እርምጃን የተመለከተው የአዋጅ ክፍል እ.አ.አ. በ2006 በወጣው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት (ተ.መ.ድ) የዓለም አቀፍ ንግድ ሕግ ኮሚሽን (UNCITRAL) ድንጋጌዎች ውስጥ የተጠቀሱትን መለያዎች ከመያዙም በላይ በብዙ ብሔራዊ የግልግል ዳኝነት ሕግጋት *(Lex arbitri)* ስለጉዳዩ ከተጠቀሰው በላይ በዝርዝር የተደነገገበት ነው ማለት ይቻላል። ምናልባትም ዝርዝር ከሆኑት ጉዳዮች መሀል ሊጠቀሱ የሚገባቸው ጉዳዮች በተ.መ.ድ. የኒውዮርክ አለምአቀፍ ስምምነት የፍርድ አፈፃፀም ጥያቄዎች ውድቅ የሚደረጉባቸውን ምክንያቶች ጨምሮ ከተደነገገው የውጭ ሀገር የግልግል ዳኝነት ፍርድ አፈፃፀም ጋር ተመሳሳይ በሆነ መልኩ የተመለከቱት የጊዜያዊ የመጠባበቂያ እርምጃ አፈፃፀም ንዑስ አንቀፆች ናቸው። እንዲህ ይላሉ፡-

---

[98] *ዝኒ ከማሁ፣* አንቀጽ 14። "የግልግል ዳኞች መቃወሚያ፡- 1/ የአንድን ዳኛ መመረጥ መቃወም የሚቻለው ገለልተኛነቱን እና ነፃነቱን ወይም በግልግል ስምምነቱ ላይ የተቀመጡ መስፈርቶችን የማያሟላ መሆኑን አሳማኝ ጥርጣሬ ውስጥ የሚከቱ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ብቻ ነው።"

[99] *ዝኒ ከማሁ፣* አንቀጽ 18።

፩/ የውጭ ፍርዶችን እውቅና ስለመስጠት እና አፈፃፀምን በተመለከተ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የተሰጠበትን ሀገር ከግምት ሳያስገባ በጉባዔ የተሰጠ ጊዜያዊ የመጠባበቂያ እርምጃ ትዕዛዝ አስገዳጅነት ይኖረዋል።

፪/ ጊዜያዊ የመጠባበቂያ እርምጃ ትዕዛዝ መፈፀም ካልቻለ አንደኛው ወገን ትዕዛዙ እንዲፈፀምለት ለፍርድ ቤት ሊያመለክት ይችላል። [100]

ጊዜያዊ የመጠባበቂያ እርምጃ እንዲፈፀም የሚቀርብ ጥያቄ ተቀባይነት የሚያጣባቸው ምክንያቶች የግልግል ዳኝነት ፍርዱ ተቀባይነት እንዳያገኝ ከሚያደርጉት ድንጋጌዎች ጋር ተመሳሳይነት አላቸው። [101] በዚህ ረገድ አዋጁ በብሔራዊም ሆነ አለም አቀፍ ደረጃ በሚሰጡ ጊዜያዊ የመጠባበቂያ እርምጃዎች መካከል ልዩነትን አያደርግም። ተዋዋይ ወገኖች ጊዜያዊ የመጠባበቂያ እርምጃ ትዕዛዝ እንዲሰጥላቸው የግልግል ዳኝነት ጉባዔውን ወይም በቀጥታ ፍርድ ቤቱን መጠየቅ እንደሚችሉ በአማራጭ ተደንግጓል። [102] እንደቻይና ባሉ አንዳንድ አገሮች ከሚደረገው በተቃራኒ በዚህ አዋጅ ተዋዋይ ወገኖች ወይ ወደ ግልግል ዳኝነት ጉባዔው አሊያም በቀጥታ ወደ ፍርድ ቤት መሄድ ይችላሉ። በቻይና የግልግል ዳኝነት ሕግ መሠረት ግን ተዋዋይ ወገን በአስገዳጅ በቅድሚያ ማመልከት ያለበት ጉዳዩን ካየ በኋላ ወደ ፍርድ ቤት ማስተላለፍ ወዳለበት ወደ ግልግል ዳኝነት ኮሚሽን ነው። [103]

---

100 ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 25(1-2)።

101 ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 26።

102 ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 27። "የግልግል ዳኝነቱ መቀመጫው በየትኛውም ቦታ ያደረገ የግልግል ዳኝነት ከግምት ሳይገባ ተዋዋይ ወገኖች የጊዜያዊ መጠበቂያ እርምጃ ትዕዛዝ እንዲሰጥላቸው ፍርድ ቤትን ሊጠይቁ ይችላሉ።" ምናልባትም አዲሱ የግልግል አዋጅ ከፀደቀበት ጊዜ ጀምሮ ለመጀመሪያ ጊዜ ለጊዜያዊ እርምጃ የቀረበው ዓለም አቀፍ ማመልከቻ በቅርቡ በኢትዮጵያ ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 275955 የቻይና ናሽናል ፔትሮሊየም ኮርፖሬሽን (BGP) በፖሊ-ጂሲኤል ፔትሮሊየም ኢንቨስትመንት ኃላፊነቱ የተወሰነ የኢትዮጵያ ቅርንጫፍ እና POLY-GCL ፔትሮሊየም ኃላፊነቱ የተወሰነ ኢንቨስትመንት (POLY-GCL) ላይ የቀረበው ማመልከቻ ነው። ፍርድ ቤቱ የቢጂፒን ጥያቄ ተቀብሎ POLY-GCL በኢትዮጵያ ኦጋዴን ክልል የሚገኘውን የነዳጅ ፍለጋና ማውጣት ፍቃድን የማስተላለፍ፣ የመሸጥ ወይም በእዳ መያዣነት የመጠቀም መብቶችን (የኮንሴሽን መብቶችን) የማገድ እና ተጠሪዎች በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያላቸው የባንክ ሂሳብ እንዲታገድ ትዕዛዝ ሰጥቷል። በሆንግ ኮንግ አለምአቀፍ የግልግል ዳኝነት የተቋቋመው አለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት የመጨረሻውን ብይን እስከሚሰጥ ድረስ የፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ፀንቶ እንደሚቆይ በግልፅ ተናግሯል።

103 Arts. 25, 68, Arbitration Law of China (promulgated by the Standing Comm. Nat'l People's Cong., Aug. 31, 1994, effective Sep. 1, 1995), 1994 STANDING COMM. NAT'L PEOPLE'S CONG. GAZ. 8 (China). Available at http://english.mofcom.gov.cn/aarticle/policyrelease/internationalpolicy/200705/20070504715852.html [https://perma.cc/KFC8-8435].

በብዙ የሕግ ሥርዓቶች ተቀባይ እንደሆነው ጊዜያዊ የመጠባበቂያ እርምጃ እንዲሰጠው ያመለከተ ወገን ዋስትና እንዲያቀርብ ሊጠየቅ ይችላል።[104] አስገዳጅ ያለመሆኑን ግን ልብ ይሏል።

### *3.2.6. በግልግል ዳኝነት ውሳኔ ላይ ሊቀርቡ ስለሚችሉ አቤቱታዎች*

#### *ሀ. የግልግል ዳኝነት ውሳኔን ስለመቃወምና ስለማሻር (Annulment)*

በግልግል ዳኝነት ውሳኔ አቤቱታ ስለሚቀርብባቸው ሁኔታዎች የሚደነግጉ ሁለት አንቀፆች በኢትዮጵያ የግልግል ዳኝነት አዋጅ ውስጥ ይገኛሉ። የመጀመሪያው "የግልግል ዳኝነት ውሳኔን ስለመቃወም" በሚል ርዕስ ስር የተደነገገው ነው።[105] ሌላው ደግሞ በስፋት የሚታወቀው የግልግል ዳኝነት ውሳኔን ስለመሻር የሚደነግገው አንቀጽ ነው።[106] ተዋዋይ ወገን ሆነም አልሆነም፣ ነገር ግን በግልግል ዳኝነቱ ሂደት ውስጥ የክርክሩ ተሳታፊ መሆን ሲገባው ያልተሳተፈ ከሆነ የግልግል ዳኝነት ውሳኔ መተላለፉን ባወቀ በ60 ቀናት ውስጥ ውሳኔውን መቃወም እንደሚችል አዋጁ ይደነግጋል።[107]

ይህ ዓይነቱ ድንጋጌ ያስፈለገበት ምክንያት በጉዳዩ ላይ የሚያገባቸው አካላት መብት ሳይከበርና የሥነ-ስርዓት ፍትህ ሳይጠበቅ የግልግል ዳኝነቱ እንዳይፈፀም ለማድረግ ነው። በተመሳሳዩም በግልግል ዳኝነቱ ጣልቃ ገብቶ የነበረ ሦስተኛ ወገን በውሳኔው ላይ ወይም በውሳኔው አፈፃፀም ላይ መቃወሚያ ማቅረብ እንደማይችሉ አዋጁ ይደነግጋል።[108] በአንቀጹ የግልባጭ ንባብ ሥርዓት (*a contrario* reading) ጣልቃ እንዲገባ አመልክቶ ያልተፈቀደለት ሦስተኛ ወገን በአዋጁ አንቀጽ 48 ንዑስ አንቀጽ 5 በተመለከተው መሠረት በፍትሐ ብሔር የሥነ-ስርዓት ሕጉ ውስጥ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ከዚህ አዋጅ እስካልተቃረኑ ድረስ የተሰጠውን የግልግል ዳኝነት ውሳኔና አፈፃፀሙን መቃወም ይችላል።[109]

---

[104] የኢትዮጵያ የግልግል አዋጅ፥ *በግርጌ ማስታወሻ ቁ.* 63 የተጠቀሰ፥ አንቀጽ 21(3)።

[105] *ዝኒ ከማሁ*፥ አንቀጽ 48።

[106] *ዝኒ ከማሁ*፥ አንቀጽ 50።

[107] *ዝኒ ከማሁ*፥ አንቀጽ 48(1)።

[108] *ዝኒ ከማሁ*፥ አንቀጽ 48(2)፡ "መቃወሚያውን የሚያቀረበው ሶስተኛ ወገን አስቀድሞ ጉዳዩን ሲመለከተው በነበረው ጉባኤ አቤቱታውን አቅርቦ በግልግል ዳኝነት ሂደቱ ጣልቃ ገብቶ ከነበረ፥ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት መቃወሚያውን ማቅረብ አይችልም።"

[109] *ዝኒ ከማሁ*፥ አንቀጽ 48(5)።.

*በግልግል ዳኝነት ውሳኔ ላይ የመቃወም አቤቱታን ለማቅረብ ተዋዋይ ወገኖችና ሦስተኛ ወገን የሚታዩት በተለያየ መንገድ ነው። የክርክሩ ተካፋይ መሆን ይገባው የነበረ ግን ያልተካፈለ ተዋዋይ ወገን የግልግል ዳኝነት ውሳኔ እንዳይፈፀም የሚቃወም ከሆነ፣ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ተመልክቶ ውሳኔውን በማሻሻል ለግልግል ዳኝነት ጉባዔው እንዲመልሰው አዋጁ ይደነግጋል። ይህ ማለት ግን አንድ የግልግል ዳኝነት ጉባዔ የመጨረሻ ውሳኔውን ከሰጠ በኋላ ህልውናው ያበቃለት ስለሚሆን (functus officio) ፍርድ ቤቱ ራሱ ጉዳዩን አይቶ የመጨረሻ ውሳኔን ካልሰጠ በቀር የሚመራለት የግልግል ዳኝነት አካል ሊኖር እንደማይችል ልብ ይሏል።* [110]

*የመቃወሚያ አቤቱታ አቅራቢው ሦስተኛ ወገን ከሆነ ግን ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በራሱ በመመርመር የግልግል ዳኝነት ውሳኔውን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ሊሽረው ወይም ሊያሻሽለው እንደሚችል አዋጁ ይደነግጋል። ይህ ማለት ደግሞ ተከራካሪ ሆኖ መቅረብ የነበረበት ወገን ሳይገባ በመቅረቱ ምክንያት የግልግል ዳኝነት ስምምነቱ ውድቅ እንደተደረገ ያስቆጥረዋል።* [111] *ሦስተኛው ወገን በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ጠይቆ ጉባዔው ጥያቄውን ካልተቀበለው፥ በአፀፋ መልኩ ፍርድ ቤቱ እጅጉን ተመጣጣኝ ባልሆነ መልኩ ጉዳዩን ሙሉ በሙሉ በማየት ፍርድ ሊሰጥ ይችላል።*

*ለማንኛውም ይህ አንቀጽ በጥንቃቄ ሲመረመር የሦስተኛ ወገን ጣልቃ መግባትን አስመልክቶ ለግልግል ዳኝነት ጉባዔውና ለፍርድ ቤቱ የተከፋፈለውን የሥልጣን ልክ በግልፅ የሚያሳይ ነው። በግልግል ዳኝነቱ ሂደት የመጨረሻ ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት መሆኑንም አመላካች ነው።*

*ሌሎች ትኩረት የሚሹ አንቀፆች ደግሞ የግልግል ዳኝነት ውሳኔን ስለመሻር የተመለከቱት ናቸው። በብዙ ሀገሮች እንዳለው የኢትዮጵያውም አዋጅ የግልግል ዳኝነት እንዳይፈፀም የሚያደርጉ ምክንያቶችን ከኒውዮርኩ ኮንቬንሽን አንቀጽ* V *ባመዛኙ የወሰደ ይመስላል።* [112]

---

[110] *ዝኒ ከማሁ፥ አንቀጽ* 48(3)።

[111] *ዝኒ ከማሁ፥ አንቀጽ* 48(4)።

[112] *ዝኒ ከማሁ፥ አንቀጽ* 50። *የዚህ ድንጋጌ የአማርኛውና የእንግሊዝኛው ቅጅ ልዩነት ያላቸው ይመስላል። ይሄ ልዩነት ታስቦበት ሳይሆን፥ የአማርኛው ጽሑፉ ቀጥታ ወደ እንግሊዘኛ ሲተረጎም የተፈጠረ ይመስላል። "ሀ)አመልካቹ ላይ ተፈፃሚነት ባለው ሕግ መሠረት የግልግል ስምምነት ለማድረግ የሚያስችለው ችሎታ የሌለው እንደሆነ፤ ለ) የግልግል ዳኝነት ስምምነቱ በተዋዋዮች በተመረጠው ሕግ ወይም በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ዋጋ የሌለውና ፈራሽ የሆነ ወይም ጊዜው ያለፈ እንደሆነ፤ ሐ) አቤቱታ አቅራቢው የግልግል ዳኞች ስለመሾማቸው፣ ስለ ግልግል ዳኝነተ ሂደቱ በቂ ማስታወቂያ ያልተሰጠው መሆኑን ሲያሳይ ወይም በሂደቱ ለመሰማት አለመቻሉን ሲያስረዳ፤ መ) የግልግል ዳኞች በሂደቱ በገለልተኛነታቸው ወይም ነፃነታቸውን*

ይህ ደግሞ ሊሆን የቻለው የኒውዮርኩ ኮንቬንሽን የግልግል ዳኝነት ውሳኔ የሚሻርባቸውን መሠረቶች ለኮንቬንሽኑ አባል አገራት ብሔራዊ ሕግጋት አሳልፎ ስለሰጠ ነው።

የግልግል ዳኝነቱ ስምምነት ከብሔራዊ ሕግ አንፃር ዋጋ የሌለውና ፈራሽ የሚሆንበትን ሁኔታ የሚደነግገው የአዋጁ አንቀጽ 50(2)(ለ) በግልፅ አሻሚ የሆነ ጉዳይ የሚታይበት ነው። እንዲህም ይነበባል፡- አንድን የግልግል ዳኝነት ውሳኔ ለማሻር አቤቱታ የሚቀርበው "የግልግል ዳኝነት ስምምነቱ በተዋዋዮች በተመረጠው ሕግ ወይም በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ዋጋ የሌለውና ፈራሽ የሆነ ወይም ጊዜው ያለፈ እንደሆነ" ነው።[113] የኒውዮርኩ ኮንቬንሽን አቻ አንቀጽ ደግሞ እንዲህ ይነበባል፡- አንድን የግልግል ዳኝነት ውሳኔ ለማሻር አቤቱታ የሚቀርበው "በተዋዋዮች በተመረጠው ሕግ መሰረት ወይም ውሳኔ በተሰጠበት ሀገር ሕግ የግልግል ዳኝነት ስምምነቱ ዋጋ የሌለውና ፈራሽ ከሆነ" ነው።[114] ምንም እንኳን ይህ የሚደረግበት ምክንያት የግልግል ዳኝነት ውሳኔ እንዳይፈፀም በሚል ሲሆን፣ በብዙ ሀገሮች ግን እነዚህ ምክንያቶች የግልግል ዳኝነት ውሳኔን ለማሻርም መሠረቶች ተደርገው የሚወሰዱ ምክንያቶች ናቸው። ኢትዮጵያም ይህንኑ አካሄድ ብትከተልም ነገር ግን በተዋዋይ ወገኖች ከተመረጠው ሕግ ውጭ በብቸኛ አማራጭነት የተጠቀሰው የኢትዮጵያ ሕግ እንጂ የግልግል ዳኝነት ውሳኔው የተላለፈበት ሀገር ሕግ አይደለም። ምናልባትም በምክንያትነት የተወሰደው የግልግል ዳኝነት ውሳኔን የማሻር ጉዳይ ስለሆነ ክርክሩ ደግሞ መካሄድ ያለበት በኢትዮጵያ ነው ከሚል ይሆናል። መሠረታዊ የሆነው አሻሚ ጉዳይ ግን የሚመነጨው ውሳኔውን በመቃወም ለማሻር መሰረት (ምክንያት) ከሆነው ጉዳይ ሳይሆን የአማራጮቹ አያያዥ ከሆነው "ወይም" ከሚለው ቃል ነው። "ወይም" የሚለው አያያዥ ቃል የሚያመለክተው ፍ/ቤቱ በራሱ ምርጫ ተዋዋዮች ከመረጡት ሕግና ከኢትዮጵያ ሕግ የፈለገውን ይመርጣል የሚል አሻሚ ትርጉምን የያዘ ነው። ምንም እንኳን የአማርኛው አንቀጽ የተከሰተውን ችግር ፈቺ ባይሆንም ሁለት ህጎችን ለምርጫ አቅርቧል። ከህጎቹ የአቀማመጥ ተዋረድ በመነሳት ሕግ አውጪው ምናልባትም ሊል የፈለገው በተዋዋዮቹ የተመረጠ የሥረ-ነገር ሕግ ከሌለ ፍርድ ቤቱ የሚተገብረው የኢትዮጵያን ሕግ ነው የሚል ሳይሆን አይቀርም።

---

ጠብቀው ውሳኔ ያልሰጡ ሲሆን ወይም ከተዋዋይ ወገኖች መደለያ በመቀበል ውሳኔ ሰጥተው ከሆነ፤ ሠ) የግልግል ዳኝነት ውሳኔው የተሰጠበት ጉዳይ ከግልግል ዳኝነት ስምምነቱ ወሰን በላይ ውሳኔ የሰጠ ከሆነ፤ ረ) የጉባዔው አመሠራረት እና በሂደቱ የተተገበረው ሥነ-ሥርዓት ከተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ወይም በዚህ አዋጅ ከተደነገገው ጋር የሚቃረን እና ውሳኔው ላይ ተጽእኖ ያሳደረ ከሆነ ነው።"

[113] የኢትዮጵያ የግልግል አዋጅ፥ *በግርጌ ማስታወሻ ቁ.* 63 የተጠቀሰ፥ አንቀጽ 50(2)(ለ)።

[114] የኒውዮርክ ኮንቬንሽን፥ *በግርጌ ማስታወሻ ቁ.* 75 የተጠቀሰ፥ አንቀጽ 5 (1)(ሀ)።

ከዚህ ጋር በተያያዘ ሊነሳ የሚገባው ጉዳይ ምንም እንኳን የኒውዮርክ ኮንቬንሽን አንድ የግልግል ዳኝነት ውሳኔን ለማሻር ሲባል ብቻ ተቃውሞ እንዲቀርብበት በመገደብ ውሳኔው የመጨረሻ መሆኑን ታሳቢ ሲያደርግ፥ የኢትዮጵያው ሕግ ግን በተወሰኑ ምክንያቶች በውሳኔው ላይ ይግባኝ ማቅረብ እንደሚቻልም ይፈቅዳል። ለዚህም ሁለት መንገዶችን ታሳቢ አድርጓል፡- (1) ተዋዋዮቹ ይግባኝ እንዲጠየቅ ከተስማሙ፣[115] ወይም (2) መሰረታዊ የሕግ ስህተት ሲኖር የሰበር አቤቱታ ማቅረብ እንደሚቻል ካልገደ።[116] በሌላ አገላለፅ፣ የግልግል ዳኝነት ውሳኔ ይግባኝ ሊባልበት እንደሚችል ተዋዋዮቹ በስምምነታቸው እስካላሰፈሩ ድረስ የመጨረሻና አስገዳጅ ነው። ህጉ ታሳቢ የሚያደርገው ሁሉም የግልግል ዳኝነት ውሳኔዎች መሠረታዊ የሕግ ስህተት ካለባቸው በፍርድ ቤት በይግባኝ ሊታዩ እንደሚችሉ ነው። ሆኖም ግን ከሚከተሉት ሦስት ሁኔታዎች በቀር ተዋዋዮቹ በስምምነት ይህን የይግባኝ መብት ማስቀረት ይችላሉ፡- (1) ውሳኔው የተሰጠው በርትዕ ወይም የታወቁ የንግድ ልምዶችን መሠረት በማድረግ ከሆነ *(ex aquae et bono)*፣[117] (2) ውሳኔው የተሰጠው በተዋዋዮቹ ስምምነት ከሆነ፣[118] እና (3) በተዋዋዮቹ ስምምነት ውሳኔ የተሰጠው ምክንያቱ ሳይገለፅ ከሆነ።[119]

በአጠቃላይ አዋጁ ከውሳኔ ማግስት ሊቀጥሉ ስለሚችሉ ክርክሮች ሰፊ መድረክን ለተከራካሪ ወገኖች የፈጠረ ቢሆንም፥ የግልግል ዳኝነት ውሳኔን የመጨረሻነት ግን በጉልህ ደንግጓል። ይሁን እንጂ በአንቀጹ 49(2)[120] ላይ የተመለከተው "መሰረታዊ የሕግ ስህተት ሲኖር" የሚለው ሐረግ የኢትዮጵያን ሕግ ብቻ፣ ወይስ የውጭ ሀገርን ሕግ አሊያም ደግሞ ሁለቱንም ስለማካተቱ ግልፅነት ይጎድለዋል። ምክንያቱም አዋጁ የውጭ ሀገር ሕግ ተፈፃሚ ሊሆን እንደሚችል ደንግጓልና።[121] በመሆኑም ሕግ የሚለው ቃል በዚህ ስፍራ የተመለከተው የውጭ ሀገሩንም ሕግ በማካተት ነው ቢባል የተሳሳተ ግምት አይደለም።

[115] የኢትዮጵያ የግልግል አዋጅ፥ *የግርጌ ማስታወሻ ቁ.* 63 የተጠቀሰ፥ አንቀጽ 40(1)።

[116] *ዝኒ ከማሁ*፥ አንቀጽ 49(2)።

[117] *ዝኒ ከማሁ*፥ አንቀጽ 49(3) ከአንቀጽ 41(5) ጋር።

[118] *ዝኒ ከማሁ*፥ አንቀጽ 49(3) ከአንቀጽ 43 ጋር።

[119] *ዝኒ ከማሁ*፥ አንቀጽ 49(3) ከአንቀጽ 44(2) ጋር።

[120] *ዝኒ ከማሁ*፥ አንቀጽ 49(2)። ("2/ ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በስተቀር መሰረታዊ የሕግ ስህተት ሲኖር የሰበር አቤቱታ ማቅረብ ይቻላል")

[121] *ዝኒ ከማሁ*፥ አንቀጽ 41(3&4) ("3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በስምምነት የተመረጠ ሕግ ከሌለ ጉባኤው ከጉዳዩ ጋር ቅርበትና አግባብነት ያላቸውን ሕጎች በመምረጥ ተፈፃሚ ያደርጋል። 4/ ጉዳዩ አለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት ይዘት የሌለው ከሆነ ጉባዔው የኢትዮጵያን ሕግ ብቻ ተፈጻሚ ያደርጋል።")

የውጭ ሀገር ሕጎችም አተገባበር በተመለከተ በተዋዋይ ወገኖች ሌላ ስምምነት እስካልተደረሰ ድረስ ለመሰረታዊ የሕግ ስህተት ይግባኝ መብት መሆኑ የውጭ ሀገር ሕግንም ያካትታል። ይህ ዓይነቱ ድምዳሜም ትክክል የሚሆነው አዋጁ ለውጭ ሀገር ሕግ የተለየ ገደብን ባለመጣሉ ነው። የውጭ ሀገር ሕግ ተፈፃሚ በሆነበት የግልግል ዳኝነት ተሸናፊው ወገን ጉባዔው የውጭ ሀገሩን ሕግ የተረጎመበትን አካሄድ ቢቃወም፥ የሰበር ችሎቱ ከትክክለኛው የውጭ ሀገር ሕግ አተረጓጎም ለመድረስ በፍትሐ ብሔር ክርክር የውጭ ሀገር ሕግ በሚመዘንበት መልኩ እንደሚመለከተው ማመን አያዳግትም። ይሁን እንጂ ተቃውሞ የቀረበበት ተፈፃሚ ሕግ ግን የኢትዮጵያ ሕግ ከሆነ፥ አሁን በኢትዮጵያ በስራ ላይ ባለው ሕገ-መንግስት መሰረት ተዋዋዮቹ የሰበር አቤቱታን በራሳቸው ስምምነት መገደብ የሚችሉ አይመስልም። ምክንያቱም በሕገ-መንግስቱ መሰረት የሰበር ችሎቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተቶችን የማረም ስልጣን ስላለው ነው። አግባብነት ያለው የሕገ-መንግስቱም አንቀጽ እንዲህ ይነበባል፡- “ሀ) የፌደራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበትን ማናቸውንም የመጨረሻ ውሳኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ስልጣን ይኖረዋል። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።”[122] ተዋዋይ ወገኖች በኢትዮጵያ ሕግ አተረጓጎም ላይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ቢፈፀም በሰበር ችሎቱ ሊታይ አይገባም በማለት መስማማት እንደሚችሉ የግልግል ዳኝነት አዋጁ አግባብነት ያላቸው አንቀፆች መፍቀዳቸው ሕገ-መንግስታዊ ነው ወይ የሚልን ጥያቄ ማስነሳቱም አይቀሬ ነው።[123]

### *ለ. ለግልግል ዳኝነት ውሳኔ እውቅና መስጠትና ውሳኔን ማስፈፀም*

በዓለም አቀፍ ማህበረሰብ አስቀድሞ እንደተፀነሰው የኒውዮርክ ኮንቬንሽን ሙሉ ዓላማው ለግልግል ዳኝነት ውሳኔ እውቅና ስለመስጠትና ውሳኔውን ስለማስፈፀም ነው። በኒውዮርክ ኮንቬንሽን የግልግል ዳኝነትን ስለማስፈፀም የሚያወሳው አንቀጽ II(3) በስምምነቱ ውስጥ የተካተተው በመጨረሻዎቹ ሰዓታት ነው። በቀጣይም በዚህ አንቀጽ ዙሪያ የተደረገው ትንተናና ክርክር የግልግል ዳኝነት ሕግ ሳይንስን አንድ ሦስተኛውን ቦታ የያዘ ሊሆን ችሏል።

---

[122] የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት፥ አንቀጽ 80(3)(ሀ)።

[123] ጠቅላይ ፍርድ ቤት *በኮንስታ ጆይንት ቬንቸር እና የኢትዮጵያ-ጅቡቲ ምድር ባቡር ኩባንያ ጉዳይ ላይ* የግልግል አዋጁ ከመጽደቁ በፊት በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት የሕግ ስህተቶችን ስለመገምገም ሰፊ አስተያየት ሰጥቷል። *ኮንስታ ጆይንት ቬንቸር ከኢትዮጵያ-ጅቡቲ የባቡር ኩባንያ* [2016] 2013-32. የሰበር አቤቱታው በተከታዩ ድረ-ገፅ ይገኛል፡- https://jusmundi.com/en/document/pdf/other/en-consta-joint-venture-v-chemin-de-fer-djibouto-ethiopien-the-ethiopian-djibouti-railway-representing-the-federal-democratic-republic-of-ethiopia-and-the-republic-of-djibouti-petition-for-cassation-review-thursday-26th-may-2016 [https://perma.cc/YP86-DYAW].

*የኮንቬንሽኑ አርቃቂ የነበሩት ሚ/ር ፒየር ሳንደርስ የዚህን አንቀጽ በመጨረሻዎቹ ደቂቃዎች ማካተት አስመልክቶ ስለነበረው አስገራሚ ታሪክ እንዲህ በማለት ፅፏል፡-*

> *የኮንቬንሽኑን ታሪክ በተመለከተ ያደረግሁት ጥናት ባብዛኛው ያተኮረው በኮንፈረንሱ ወቅት 'የደች ፕሮፖዛል' በመባል በሚታወቀው ጉዳይ ላይ ይሆናል። ሐሳቡ የተፀነሰው ኮንፈረንሱ በተጀመረበት በመጀመሪያው ሳምንት ላይ ነበር። ከኒውዮርክ ወጣ ብላ በምትገኝ መለስተኛ ከተማ በሚገኘው የአማቴ ቤት ቅዳሜና እሁድን ለማሳለፍ በዚያ ነበርኩ። አንዲት ትንሽ ተንቀሳቃሽ መተየቢያ በጉልበቴ ላይ አድርጌ በግቢ ውስጥ ተቀምጬ ስሰራ አሁን ድረስ ይታየኛል። ከዚያ ስፍራ ነው አንድ ቀን ፀሀይ እየሞቅሁ ሳለ በኋላ 'የደች ፕሮፖዛል' በመባል የታወቀው ሀሳብ የተፀነሰው። ... በኮንፈረንሱም ማጠናቀቂያ ሰዓት ላይ ነው ይህ አሁን አንቀጽ* II *ሆኖ የወጣው ስለግልግል ዳኝነት ስምምነት የሚያወሳው አንቀጽ እንዲካተት የተደረገው።* [124]

*ኮንቬንሽኑ የተፀነሰበትና የተዋቀረበት ዋና ዓላማ የነበረው በአንቀጽ* III *እና* V *ስር ስለተካተቱት ለውጭ ሀገር የግልግል ዳኝነት ውሳኔ እውቅና ስለመስጠትና ስለማስፈፀም ነበር። ኢትዮጵያ ዘግይታም ቢሆን በቅርቡ ያፀደቀችውን ኮንቬንሽን ተከትሎ ያወጣችው አዋጅም እነዚህኑ የኮንቬንሽኑን አይነተኛ አንቀፆች የተወሰኑ ማሻሻያዎች በማድረግ አካትታቸዋለች። በአንቀፆቹ ላይ ግን ማሻሻያዎቹን ለምን ማድረግ እንዳስፈለገ ግልፅ አይደለም። ቁልፍ የሆነው አግባብነት ያለው አንቀጽም እንዲህ ይነበባል፡- "፩/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፺ ወይም ፺፪ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በኢትዮጵያም ሆነ በውጭ ሀገር የተሰጠ የግልግል ዳኝነት ውሳኔ አስገዳጅ እንደሆነ ተቆጥሮ ጉዳዩ በፍርድ ቤት ቢታይ ኖሮ ፍርዱን ሊያስፈፅም ለሚችለው ፍ/ቤት በማቅረብ በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ መሠረት የፍርድ ውሳኔ በሚፈፅምበት አኳኋን ይፈፀማል።"*[125]

*የአዋጁ አንቀጽ* 52(1) *ደግሞ እንዲህ ይላል፡- "የግልግል ዳኝነት ውሳኔ እንዳይፈፀም መቃወም የሚቻለው ከዚህ በፊት ውሳኔው እንዲሻር ለፍርድ ቤት አቤቱታ ቀርቦ ውድቅ ያልተደረገ ከሆነ ነው።" የአማርኛው ገዢ አንቀጽ በትክክል ስለመቀመጡ ልብ ይሏል። በሌላ አገላለፅ ውሳኔው እንዳይፈፀም የመቃወም እድል የሚገኘው ውሳኔው እንዲሻር የተደረገው ጥረት ውጤታማ ካልሆነ ብቻ ነው። አቀራረፁ ታሳቢ ያደረገውም ውሳኔን ማሻርና ውሳኔን*

---

[124] Pieter Sanders, The Making of the Convention, in U.N., ENFORCING ARBITRAL AWARDS UNDER THE NEW YORK CONVENTION: EXPERIENCE AND PROSPECTS, U.N. Sales No. E. 99. V. 2, 3-4 (1999), http://www.newyorkconvention.org/travaux+preparatoires [https://perma.cc/P8EB-CTKM].

[125] *የኢትዮጵያ የግልግል አዋጅ፣ በግርጌ ማስታወሻ ቁ.* 63 *የተጠቀሰ፣ አንቀጽ* 51(1)።

እንዳይፈፀም መቃወም ተከታትለው እንዲመጡ ነው። ይሁን እንጂ ሁለቱም አቤቱታዎች በአንድ ጊዜ በሁለቱ ወገኖች ሊጀመሩ እንደሚችሉ ከግምት አልገባም። በተግባር በተደጋጋሚ እንደሚታየው ተሸናፊው ወገን ውሳኔውን ለማሻር ወደ ፍርድ ቤት ሲሄድ፥ አሸናፊው ወገን ደግሞ ውሳኔውን ለማስፈፀም እንዲሁ ወደ ፍርድ ቤት ይሄዳል። ውሳኔን መቃወም የሚቻለው ውሳኔውን ለማሻር የቀረበው አቤቱታ ውድቅ ከተደረገ ነው የሚለው እሳቤ ውሳኔው ከተሻረ ውሳኔ ሊፈፀም አይችልምና እንዳይፈፀም ተቃውሞ የማቅረቡን ጉዳይ ዋጋ ቢስ ያደርገዋል።

ሌላው በአዋጁ ለውጥ የታየበት ጉዳይ የግልግል ዳኝነት ስምምነትን የፀና መሆን አለመሆን የሚወስነው ሕግ የትኛው መሆን አለበት የሚለው ምርጫ ነው። በኒውዮርክ ኮንቬንሽን አንቀጽ V(1)(ሀ) ላይ የግልግል ዳኝነት ውሳኔ ሊፈፀም የማይችለው "ስምምነቱ በተዋዋዮቹ በተመረጠው ሀገር ሕግ የማይፀና ከሆነ፣ ወይም ስምምነቱ ስለተመረጠው ሀገር ሕግ የማያነሳ ከሆነ ደግሞ የግልግል ዳኝነቱ ውሳኔ በተሰጠበት ሀገር ሕግ ስምምነቱ የማይፀና ከሆነ ነው።"[126] በመሪነት የሚተገበረው ተፈፃሚ ሕግ "የግልግል ዳኝነቱ ውሳኔ የተሰጠበት ሀገር ሕግ" ነው። የኢትዮጵያው የግልግል ዳኝነት አዋጅ ግን ውሳኔው የትም ሀገር ይሰጥ ይህን በመሪነት የሚተገበረውን ተፈፃሚ ሕግ እንዲህ በማለት በኢትዮጵያ ሕግ ተክቶታል፤ "የግልግል ዳኝነት ስምምነቱ በተዋዋዮቹ በተመረጠው ሕግ ወይም በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ዋጋ የሌለውና ፈራሽ የሆነ ወይም ጊዜው ያለፈ እንደሆነ"።[127] ይህ ዓይነቱ አቀራረፅ ምን የተለየ ጠቀሜታን እንደሚያስገኝ ግን ግልፅ አይደለም።

ሌላው ግልፅ የሆነ ለውጥ የተደረገበት አንቀፅ የሚገኘው በአዋጁ አንቀጽ 52(2)(ረ) ላይ ነው። እንዲህም ይነበባል፦ "ረ/ የግልግል ዳኝነት ውሳኔው የመጨረሻ ደረጃ ላይ ያልደረሰ ከሆነ፥ የተሻለ ወይም ውሳኔው የታገደ ከሆነ።" ይህ ከኒውዮርክ ኮንቬንሽን አንቀጽ V(1)(2) ጋር ተመሳሳይነት እንዲኖረው ሆኖ የተቀረፀ ነው። "ሠ/ ውሳኔው በተከራካሪ ወገኖች ላይ ገና አስገዳጅ ካልሆነ፣ ወይም ከተሻረ፣ አሊያም ውሳኔው በተሰጠበት ሀገር ሕግ ስልጣኑ ባለው ፍ/ቤት ከታገደ።" አዋጁ እገዳንና መሻርን በመነጣጠል በተለያዩ አንቀፆች ሲይዛቸው ውሳኔውን ለመቃወም ደግሞ እንደተጨማሪ መሠረት መሰረዝን ያነሳል። አዋጁ በይግባኝ ሊገኝ የሚችልን መሻር ከግምት ሲያስገባ ኮንቬንሽኑ ግን ውሳኔው የመጨረሻ እንዲሆን ታሳቢ ያደረገ በመሆኑ በይግባኝ የሚገኝ መሰረዝን ከግምት አላስገባም። አርቃቂዎቹ ምናልባትም መሰረዝ (reversal) የሚለውን ቃል ሲጠቀሙ መሻር (set aside) የሚለውን ለመግለፅ ይሆናል። ምንም እንኳ የቃላቱ ትርጉም አንዱ ሌላውን የሚገልፅ ቢሆንም፥ ከላይ

---

[126] የኒውዮርክ ኮንቬንሽን፥ *በግርጌ ማስታወሻ ቁ.* 75 የተጠቀሰ፥ አንቀጽ 5 (1)(ሀ)።

[127] የኢትዮጵያ የግልግል አዋጅ፥ *በግርጌ ማስታወሻ ቁ.* 63 የተጠቀሰ፥ አንቀጽ 51(2)(ሀ)።

እንደተገለፀው መሻርንና ተቃውሞን የያዙ የተለያዩ አንቀፆች መኖራቸው የሚያመለክተው ስለይግባኝ በሚያወሱት አንቀፆች በመሠረታዊ የሕግ ስህተት ምክንያት ወይም በሌላ ምክንያት የሚወሰን መሰረዝ (reversal) በይግባኝ የተወሰነ መሰረዝ (appellate reversal) ነው። ይሁን እንጂ ይህን ማለት ደግሞ የተቃውሞውን ጉዳይ ዳግም እንደማንሳት ማለት ነው።

ምንም እንኳን ከላይ ያነሳናቸው ጉዳዮች ለሀገር ውስጥ የግልግል ዳኝነቶች ብቻ ተብለው የተቀረፁ ባይሆንም፥ አዋጁ በአንቀጽ 53 ላይ "በውጭ ሀገር ለተሰጠ የግልግል ዳኝነት ውሳኔ እውቅና ስለመስጠትና አፈፃፀሙ" በሚል ራሱን የቻለ ሰፊ አንቀጽ ይዟል። ይህም አንቀጽ ቢሆን ከኒውዮርክ ኮንቬንሽኑ አቻ አንቀጽ ጋር ሲተያይ የጎላም ባይሆን መጠነኛ ለውጥን ይዟል። ሊነሱ ከሚገባቸው ጥቂት ለውጦች ውስጥ የሚከተሉትን ማንሳት ይቻላል። በውጭ ሀገር ለተሠጠ የግልግል ዳኝነት ውሳኔ እውቅና ስለመስጠትና አፈፃፀሙ የሚያወራው አንቀጽ ከአስገዳጅ አቀራረጽ ላላ ወዳለው የፈቃጅነት (የአማራጭ) አቀራረፅ አዘንብሏል። በተቃራኒው ደግሞ እንዲፈፀም ለፍርድ ቤት የሚቀርብን ጥያቄ የተመለከተው አንቀጽ ደግሞ ላላ ካለው የፈቃጅንት (የአማራጭ) አቀራረፅ ወደ አስገዳጅ አቀራረፅ አዘንብሏል። ይህን በተሻለ መንገድ ለማስረዳት የሚከተሉትን ሁለት አንቀፆች በንፅፅር ማየት ይበጃል።

የአዋጁ አንቀጽ፡-

> በውጭ ሀገር የተሰጠ የግልግል ዳኝነት ውሳኔ ኢትዮጵያ ባፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የሚወድቅ ከሆነ በስምምነቱ መሠረት <u>እውቅና ሊሰጠው</u> ወይም ሊፈፀም <u>ይችላል</u>።[128]

የኒውዮርክ ኮንቬንሽን አንቀጽ፡-

> እያንዳንዱ ተዋዋይ ሀገር የግልግል ዳኝነት ውሳኔዎች አስገዳጅ እንደሆኑ <u>ይቀበላል</u>፤ በቀጣዮቹ አንቀፆች በተመለከቱት ሁኔታዎች መሰረት ውሳኔዎቹ በተላለፉበት ሀገር የሥነ-ሥርዓት ሕግ መሠረት እንዲፈፀሙ <u>ያደርጋል</u>።[129]

በውሣኔ ላይ ሊሰጥ የሚገባን እውቅና አለመቀበልና አለመፈፀምን የሚመለከቱ አንቀፆች ላይ የተስተዋለውን ለውጥ እንደሚከተለው በንፅፅር ማሳየት ይቻላል።

---

[128] *ዝኒ ከማሁ*፥ አንቀጽ 53(1)።

[129] የኒውዮርክ ኮንቬንሽን፥ *በግርጌ ማስታወሻ ቁ.* 75 የተጠቀሰ፥ አንቀጽ III።

የአዋጁ አንቀጽ 53፣ ንዑስ-አንቀጽ 2፡-

> በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በውጭ ሀገር የተሰጠ የግልግል ዳኝነት ውሳኔ <u>እውቅና ላይሰጠው</u> ወይም <u>ላይፈፀም</u> የሚችለው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው።

የኒውዮርክ ኮንቬንሽን አንቀጽ

> የግልግል ዳኝነት ውሳኔ <u>እውቅና ላይሰጠው</u> ወይም <u>ላይፈፀም የሚችለው</u> በተሸናፊው ወገን ጠያቂነት እውቅና እንዲሰጥና እንዲፈፀም ጥያቄው በቀረበበት ቦታ ላለና ሥልጣኑ ላለው አካል ቀርቦ የሚከተሉት ከተረጋገጡ ነው።

የአዋጁ የአንቀጽ አቀራረፅ እንዲያው በቀላሉ አስገዳጅ የሆነውን በአማራጭ ቃል የመተካካት ብቻ አይደለም። ወደፊት አሁን ያልታዩ ክርክሮችን የሚያስነሱ ከመሆናቸውም በላይ እነዚህ ለውጦች እንዲካተቱ አስገዳጅ የነበሩ የፖሊሲ ጉዳዮች ስለመኖራቸው የሚታወቅ ነገር የለም። ወደፊት በጉዳዩ ላይ የሚፃፉ መጣጥፎች በቀጣይ የሚመለከቱት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፥ ላሁኑ የመቃወሚያ ምክንያቶች ተብለው በተዘረዘሩት አንቀፆች ውስጥ አንዳንድ ለውጦች መደረጋቸው ሁኔታዎችን ቀላል አላደረጓቸውም ቢባል ሚዛናዊ ነው።

የኒውዮርክ ኮንቬንሽን አንቀፅ V(1) አቀራረፅ የዓለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት ሥርዓት ማጠንጠኛ በሆነ ነጥብ ላይ የተመሰረተ ነው፡- “[የግልግል ዳኝነት] ውሳኔ እውቅና ላይሰጠው ወይም ላይፈፀም የሚችለው በተሸናፊው ወገን ጠያቂነት እውቅና እንዲሰጥና እንዲፈፀም ጥያቄው በቀረበበት ቦታ ላለ ሥልጣኑ ላለው አካል ቀርቦ የሚከተሉት ከተረጋገጡ ነው።”[130] በዚህ አንቀጽ ውስጥ የአስገዳጅነት መገለጫ ከሆነው በእንግሊዘኛው “Shall” ከሚለው ቃል ይልቅ አስገዳጅ ያልሆነው “May” የሚለው የእንግሊዘኛው ቃል በጥቅም ላይ መዋሉ በመላው አለም ሰፊ ክርክርን አስነስቷል። አዲሱ አዋጅ በስፋት ተቀባይነትን ካገኘው አካሄድ የሚርቅ ከሆነ፣ አከራካሪ የሆነውን ጉዳይ የሚፈታ ነው ተብሎ ሊጠበቅ ይችላል። የሚያሳዝነው ግን የኢትዮጵያው አዲሱ አዋጅ ይህ አከራካሪ የሆነውን ጉዳይ ካለመፍታቱም በላይ ይልቁንም፥ ሆን ተብሎ ላይሆን ይችላል፥ ጉዳዩን ይበልጥ ውስብስብ አድርጎታል።

በኮንቬንሽኑ አንቀጽ ውስጥ የተቀመጠው የአስገዳጅነት ትርጉምን ባልያዘው “… may be refused” በሚለው ሀረግ ዙሪያ ያለውን ክርክር በቅድሚያ እንመልከት። ክርክሩ በአብዛኛው የሚነሳው ውሳኔው በተሰጠበት ሀገር የተሻረን በውጭ ሀገር የተሰጠ የግልግል ዳኝነት ውሳኔ

[130] ዝኒ ከማሁ፥ አንቀጽ V(1)፥ አጽንዖት ተጨምሮበታል።

ከማስፈፀም ጋር በተያያዘ ጉዳይ ላይ ነው። [131] በዚህ ጉዳይ ላይ ሁለት የአመለካከት ጎራዎች ተከስተዋል። የመጀመሪያው ጎራ አስገዳጅ ያልሆነው "May" የሚለው ቃል ውሳኔው የተሰጠበትን ሀገር በጉዳዩ ላይ የሚኖረውን አቋም ከግምት ሳያስገባ የግልግል ዳኝነት ውሳኔ ሊፈፀም ይገባል የሚል ነው። [132] ሁለተኛው ጎራ ደግሞ ለቃሉ ትርጉም ቦታ ሳይሰጥ ውሳኔው በተሰጠበት ሀገር የተሻረ ውሳኔ ሊፈፀም አይገባም የሚል አቋምን የያዘ ነው። [133] ከሁለቱ ጎራዎች መካከል የትኛው ይበልጥ ተቀባይነት እንዳገኘ እንኳ ከመግባባት አልተደረሰም።

በኢትዮጵያው አዋጅ በአንቀጹ አቀራረፅ ላይ የተደረገው ለውጥ እነዚህን መፍትሄ ያላገኙ ክርክሮች ያለመፍትሔ እንዲቀጥሉ ከማድረጉም በላይ የግልግል ዳኝነት ከብሔራዊ ሕግ በላይ ነው የሚልን አቋም የሚያራምዱ ደጋፊዎች የሚያቀነቅኑትን አይነት የተለየ አመለካከት እንዲይዙ ሊጋብዝ ይችላል። [134]

አዋጁ ተቃውሞን በተመለከተው አንቀጽ ውስጥ ሌሎች ለውጦችን አካቷል። በመጀመሪያ ምንም እንኳ ኢትዮጵያ የኒውዮርክ ኮንቬንሽንን ለመቀበል በአስገባችው የማፅደቂያ ሰነድ ውስጥ የእንካ ለእንካ መርህን ብታስመዘግብም በአዋጁም ውስጥ እራሱን የቻለ የእንካ ለእንካ መርህን ንዑስ አንቀጽ ቀርፃለች። [135] ምናልባትም ሕግ አውጪው ሌሎች ባለሁለትዮሽ ወይም በአሁን ሰዓት ያሉ ወይም ወደፊት የሚፈረሙ አለም አቀፍ ስምምነቶችን ታሳቢ አድርጎ ሊሆን ይችላል። ከዚህ በመነሳት ጉዳዩ መደጋገሙ ብዙም አሳሳቢ ላይሆን ይችላል።

በሁለተኛ ደረጃ አዋጁ በኒውዮርክ ኮንቬንሽን በአንቀጽ V(1)(መ) ላይ "የጉባኤው አመሰራረትና በሂደቱ የተተገበረው ሥነ-ሥርዓት ከተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ጋር የሚቃረን፣

[131] የአንቀጽ V(1) አጠቃላይ ድንጋጌና የአንቀፅ V(1) (e) ጥምር ንባብ። የአንቀጽ V(1)(e): "ብይኑ በተዋዋይ ወገኖች ላይ ገና አስገዳጅ ካልሆነ ወይም ብይኑ በተሰጠበት ሀገር በሚመለከተው ባለስልጣን ወይም በሀገሪቷ ሕግ የማይፀና ወይም የታገደ ከሆነ።") *ዝኒ ከማሁ።*

[132] ለምሳሌ የሚከተለውን የፍርድ ጉዳይ ይመልከቱ:- Chromalloy Aeroservices Inc. v. Ministry of Def. of Republic of Egypt, 939 F. Supp. 907 (D.D.C.1996) (ከግብፅ ውጭ የተሰጠ የግልግል ውሳኔ እንዲፈፀም አድርጓል።) ይኸው ፍርድ ቤት አቋሙን በኋላ ቀይሯል። የሚከተለውን የፍርድ ጉዳይ ይመልከቱ:- Termorio S.A.E.S.P. v. Electranta S.P., 487 F.3d 928 (D.C. Cir. 2007). Termorio SAESP v. Electranta SP. 487 F.3d 928 (DC Cir. 2007).

[133] ስለዚህ የአስተምህሮ የበለጠ ማብራሪያ ይህን መፅሐፍ ያንብቡ:- EMMANUEL GAILLARD, LEGAL THEORY OF INTERNATIONAL ARBITRATION (2010). ፀኃፊው የተለያዩ ንድፈ ሐሳቦችን ካቀረበ በኋላ የራሱን አስተያየት አስቀምጧል። *ገፅ* 24።

[134] *ዝኒ ከማሁ።*

[135] የኢትዮጵያ የግልግል አዋጅ፣ *በግርጌ ማስታወሻ ቁ.* 63 የተጠቀሰ፣ አንቀጽ 53(2)(ሀ)።

*ወይም የግልግል ዳኝነቱ ከተካሄደበት ሀገር ሕግ ጋር የሚቃረን ከሆነ"*[136] *የሚለውን ድንጋጌ በሚከተለው ቀይሮታል፡- "የግልግል ዳኝነት ውሳኔው በማይፀና የግልግል ዳኝነት ስምምነት መሠረት ወይም ውሳኔው የተሰጠበት ሀገር ሕግ በሚፈቅደው መሠረት ባልተቋቋመ ጉባዔ የተሰጠ እንደሆነ"።* [137]

*የማይፀና የግልግል ዳኝነት ስምምነት አንቀጽንና የጉባዔውን አመሠራረት ሕጋዊነት በአንድነት ከማዋሃዱም በላይ የግልግል ዳኝነት ጉባዔውን አመሠራረት ሕጋዊነት ለመወሰን የሚያስችለውን ገዢ ሕግ ከተዋዋይ ወገኖች ምርጫ ወደ ተፈፃሚው ሕግ ቀይሮታል። እንዲሁ ሲታይ የማይጎዳ ቢመስልም የተዋዋዮቹ ስምምነትና ተፈፃሚው ገዢ ሕግ ሲተገበሩ ወደተለያዩ ውጤቶች የሚመሩ ከሆነ አላስፈላጊ ወደሆነ አተካራ የሚከት ይሆናል።*

*ሦስተኛ፥ አዋጁ በኒውዮርክ ኮንቬንሽን የሌለ አዲስ አንቀጽን አካቷል። እንዲህም ይላል፡- "የተሰጠው ውሳኔ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ሊፈፀም የማይችል እንደሆነ"።* [138] *እንዲሁ ሲታይ ይህ አንቀጽ በትርጉሙ በኮንቬንሽኑ አንቀጽ* V(2)(ለ) *ላይ በልዩነት የተመለከተውን የሕዝብ ሞራልን ጉዳይ የያዘ ይመስላል። ይሁን እንጂ አዋጁ እራሱን በቻለው በአንቀጽ* 53(2)(ረ) *ላይ እንዲያውም የብሔራዊ ፀጥታን ጉዳይ የሕዝብ ሞራል አካል አድርጎ ቀርፆታል።* [139]

*እነዚህ ከላይ የተነሱት አንኳር ጉዳዮች በኒውዮርክ ኮንቬንሽን ላይ የተደረጉ ዓይነተኛ ለውጦች ናቸው። እያንዳንዱ ለውጥ የተደረገበት የፖሊሲ ምክንያት ካለ የአዋጁን አንቀፆች ብቻ በመመርመር በቀላሉ መለየት አይቻልም።*

## ማጠቃለያ

*ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ኢትዮጵያ ድንበር ተሻጋሪ የኢኮኖሚ ሕጎቿን በማዘመን ረገድ ጥሩ እመርታን አስመዝግባለች። በንግድ ዘርፍ የአለም የንግድ ድርጅትን ለመቀላቀል ድርድሮችን ጀምራለች። ግዙፉን የአፍሪካን ነፃ የንግድ ቀጣና ፕሮጀክት በሀሴት ተቀላቅላለች። ምንም እንኳን እ.አ.አ. ከ*2010 *ጀምሮ የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ጥበቃ ስምምነቶችን ማፅደቅን*

---

[136] የኒውዮርክ ኮንቬንሽን፥ *በግርጌ ማስታወሻ ቁ.* 75 የተቀመጠ፥ አንቀጽ 5(1)(መ)።

[137] የኢትዮጵያ የግልግል አዋጅ፥ *በግርጌ ማስታወሻ ቁ.* 63 የተጠቀሰ፥ አንቀጽ 53(2)(ለ)።

[138] *ዝኒ ከማሁ፥* አንቀጽ 53(2)(ሐ)።

[139] *ዝኒ ከማሁ፥* አንቀጽ 53 (2) (ረ)። ("የውሳኔውም አፈፃፀም የህዝብ ሞራል፣ ፖሊሲ እና የህዝብ ደህንነት የሚቃረን እንደሆነ ነው")።

*ዘግየት ብታደርግም፥ አዲስ የኢንቨስትመንት ሕግ በማወጅ አንድ እርምጃን ወደፊት ተራምዳለች። የድንበር ተሻጋሪ ንግድን በተመለከተም የኒውዮርክ ኮንቬንሽንን በማፅደቅ ሁሉን አቀፍ ማስፈፀሚያ የሆነውን ሕግም አውጃለች። በዚህ መጣጥፍ ለማድረግ የሞከርነው እነዚህን አዳዲስ እድገቶች አጠር ባለ መልኩ በሀያሲ እይታ ለመቃኘት ነው።*

*በእያንዳንዱ ዘርፍ ላይ በጉልህ የታየው የጋራ የሆነው ገላጭ ባህርይ በግልፅ ባልታወቁና አሳማኝ ባልሆኑ ምክንያቶች በአብዛኛው ተቀባይነትን ካገኙ መርሆዎችና አንቀፆች በተደጋጋሚ የመራቅ ወይም የመለየት ጉዳይ ነው። ይህም ከላይ ባየናቸውና በመረመርናቸው ሕግጋት ውስጥ ተከስተዋል። በዚህ ረገድ የአለም የንግድ ድርጅትን ለመቀላቀል መሟላት የሚገባቸውን መመዘኛዎች ባለማሟላት የታየው እጅጉን የማርፈድ ሁኔታ፥ የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ጥበቃ ስምምነቶች የማፅደቅ ሂደት በዝምታ የመገታቱ ጉዳይ እና ዓይነተኛ የሆኑ የኒውዮርክ ኮንቬንሽን አንቀፆችን በግልፅ የለወጡ አንቀፆች በአዲሱ የግልግል ዳኝነት አዋጅ ውስጥ መካተታቸው ሊጠቀሱ የሚገባቸው ናቸው።*

*ምናልባትም ከማንኛውም የሕግ ዘርፍ ውስጥ የድንበር ተሻጋሪ የኢኮኖሚ ሕግጋትን የማዘመን ስራ ዋና ዓላማው የየሀገሮች ድንበር ተሻጋሪ ሕግጋት በተቻለ መጠን የተጣጣሙና እንዲዋሃዱ ማድረግ በመሆኑ በማርቀቅ ሂደት ውስጥ በተጓዳኝ ሊታዩ የሚገባቸውን ለውጦች ታሳቢ ያደረገ ሊሆን ይገባ ነበር። እነዚህ ሕግጋት ድንበር ተሻጋሪ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች የሚፈልጓቸውን ሥርዓትና ተገማችነት እውን እንዲሆን ያደርጋሉ። በስፋት ተቀባይነትን ባገኙ መርሆዎችና የሕግ አንቀፆች ላይ በማያስፈልግ መልኩ በሀገር ውስጥ በተናጠል ለውጥ የሚደረግባቸው ከሆነ የማዘመን እና የማጣጣም ወይም የማዋሀድ ሥራውን የሚያኮላሽ በመሆኑ ሕጋዊ፣ ሚዛናዊ፣ የሚታይ እና የሚያስጠብቋቸው ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ወይም ሌሎች አይነት ብሔራዊ ግቦችን የማያራምዱ እስከሆነ ድረስ ሊወገዱ ይገባል።*

* * *

# THE STATE OF ETHIOPIA'S TRANSNATIONAL ECONOMIC LAW: TRADE, INVESTMENT, AND ARBITRATION

*Zewdineh Beyene Haile & Won L. Kidane*[*]

**Abstract**

*This article offers a critical appraisal of the evolution and the current state of Ethiopia's transnational economic laws focusing on trade, investment and commercial dispute settlement. It finds with curiosity a considerable degree of departure from established texts for reasons that are not readily evident and recommends limiting such departures to the promotion of legitimate, rational, ascertainable, and defensible economic, social or other types of local objectives.*

**Key-terms**: Investment, arbitration, international trade, BITs, Ethiopia

***

[*] Zewdineh Beyene Haile (PhD, SJD) and Prof. Won L. Kidane (JD, SJD) are founders and co-principals of Addis Law Group LLP (ALG), a Washington D.C. based law firm specializing mainly in international commercial and investment arbitration. For details, please see the firm's website at www.addislawgroup.com